ዲላ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ ዕጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ ፍተሻ፤ በአርባ ምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተተኳሪነት

(የአርት ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)

በአንጓች አየለ

ሰኔ 2013 ዓ.ም

ዲላ

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

የአማርኛ ቋንቋና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የአማርኛ ቋንቋ ዕጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ ፍተሻ፤ በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተተኳሪነት

በአንጓች አየለ

አማርኛን በማስተማር የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ነጥቦች በከፊል ለማሟላት ለአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት

የጥናቱ አማካሪ

እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)

ሰኔ 2013 ዓ.ም

ዲላ

የምርምር ጥናትና ወጥነት ማረጋገጫ

ይህ ጥናት "የአማርኛ ቋንቋ ዕጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ ፍተሻ፤ በአርባ ምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ አማርኛን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ሲሆን፤ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ፤የራሴ ወጥ ስራ መሆኑና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በዋቢነት መጠቀሳቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- አንጓች አየለ

ፊርማ፡- ……………………………..

ቀን፡- ………………………………

ምስጋና

ከሁሉ በፊት በብዙ ውጣ ውረዶች መካከል ደግፎ ለዚህ ያበቃኝ ቅዱስ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡በመቀጠል አማካሪዬ ዶክተር እንግዳ ዘውዴ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የጥናቱን ረቂቅ በየጊዜው በጥንቃቄ በማንበብ በማረምና ገንቢ ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን በመጠቆምና አቅጣጫ በማሳየት ስለደገፉኝ ከልብ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለዚህ ጥናት መሳካት መረጃ የመሰብሰብና የማረም ሂደቱን ላስተባበሩልኝ መምህር እምሻው ማሞ፣ የተለያዩ ማጣቀሻ መጽሐፍትን እና ሌሎችንም አስተያየቶች በማከል ለደገፉኝ ለዶክተር ኃይላይ ተስፋይ እና ለወንድሜ ፀጋዘአብ አየለ ምስጋዬ የላቀ ነው፡፡

በመጨረሻም በተለይ በማሕበራዊ ኑሮዬ ውጥረት ሲያጋጥመኝ አይዞሽ በርቺ በማለት ከጎኔ ላልተለዩኝ ቤተሰቦቼ እና ልጆቼን በመንከባከብ፣እንድሠራ ምቹ ሁኔታ ለፈጠረልኝና ሁሉን ቻይ ለሆነው በመጻፍም ሆነ በማንበብ ከጎኔ ላልተለየኝ ባለቤቴ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማውጫ **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ 1
1.2. አነሳሽ ምክንያት 3
1.3. የጥናቱ ዓላማዎች 4
1.4. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ፡- 4
1.7. የጥናቱ ወሰን 5
ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን 7
2.1 የጽህፈት ክሂል 7
2.2 ጽህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት 8
2.3 የተዋጣለት/ጥሩ ጽሁፍ 10
2.4 የጽሁፍ ክሂል መማር ጠቀሜታ 12
2.5 የጽሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች እና መልመጃ አዘገጃጀት 13
2.5.1 የጽሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች 13
2.6 የመጻፍ ክሂል መመዘኛዎች 16
ምዕራፍ ሦስት፤የአጠናን ዘዴ 20
3.1 የጥናቱ ንድፍ 20
3.2 የጥናቱ ዘዴ 20
3.2.1 የተማሪና የተምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ዘዴ 20
3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ 21
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ 24
3.4 ደረጃ አሰጣጥ 24
ምዕራፍ አራት፤የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ 26
4.1 የመረጃ ትንተና 26
4.1.1 የይዘት ስፋትና ጥልቀት መፈተሽ 26

4.1.2 የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት መመርመር 28
4.1.3 የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መፈተሽ 31
4.1.4 የሰዋስዋዊ ትክክለኛነት እና የአጻጻፍ ሥርአታቸውን መፈተሽ 33
4.2 የውጤት ማብራሪያ 39
ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት 43
5.1 ማጠቃለያ 43
5.2 አስተያየት 43
ዋቢ ጽሁፎች 45
አባሪዎች 48

የሰንጠረዥ ማውጫ ገጽ

ሰንጠረዥ 1፡ የጽሁፍ ችሎታ ደረጃ መወሰኛ 25
ሰንጠረዥ 2፡ እጩ መምህራን በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የይዘት ስፋትና ጥልቀት በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ 26
ሰንጠረዥ 3 እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ 29
ሰንጠረዥ 4 እጩ መምህሩኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀማቸው በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ 31
ሰንጠረዥ 5 እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቋንቋውን ህግ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት በተመለከተ ደረጃ ማሳያ 33
ሰንጠረዥ 6 እጩ መምህራኑ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ስርአተ አጻጻፋቸውን በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ 35
ሰንጠረዥ 7 የእጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ደረጃ ማሳያ 37
ሰንጠረዥ 8፡ እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ትንተና ማሳያ። 39

የሰዕል ማውጫ

ስዕል. 1 ሂደታዊ ጽሁፍ እንደ Coffin, Curry እና ሌሎች (2005፡34) 14
ስዕል. 2 የጥነቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ሂደት 23
ስዕል. 3 የእጩ መምህራኑ ደረጃ ማሳያ 38

አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ እጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ መፈተሽ ነው፡፡ጥናቱ የተካሄደው በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ሲሆን በናሙናነት የተመረጡት በ2012 ዓ.ም የሦስተኛ አመት ተመራቂ እጩ መምህራን ናቸው ፡፡ተጠኝ እጩ መምህራኑ በቁጥር 45 ሲሆኑ በአንድ ቡድን የተደራጁ መሆናቸውና ቁጥራቸው ትንሽ በመሆኑ ጠቅላይ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ሁሉም አባል ተጠኝ ሆነው ተመርጠዋል ፡፡የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ቅኝታዊ ገላጭ ንድፍ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ለዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ነው፡፡በድርሰት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና የተሰበሰቡ መረጃዎች በዋናነት አይነታዊ በደጋፊነት መጠናዊ ዘዴ በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ የተገኘው ውጤትም በእያንዳንዱ የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች መካከል ከይዘት ውጭ የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ሰዋስው አጠባበቅ እና ስርአተ አጻጻፍ ላይ የተመዘገበው ውጤት ዥቅተኛ መሆኑ በጥናቱ ተረጋገጧል፡፡ በፈተና የጠገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግ ኮሌጁ ያስቀመጠውን የውጤት መወሰኛ በመጠቀም ደረጃ መስጠት ተሞክሯል፡፡ ይህውም ከመቶ 61% ዝቅተኛ 36.6% መካከለኛ 2.4% ጥሩ በሚል ተለይቷል፡፡ይህም የሚያሳየው ሰፊውን ቦታ የያዘው በዝቅተኛ ደረጃ የተመዘገበው ውጤት ነው፡፡በአጠቃላይ ጥናቱ ውጤት የሚያመላክተው የእጩ መምህራኑ በአምስቱም የመጻፍ ንዑሳን ክሂሎች የተመዘገበው ዥቅተኛ ውጤት ሲሆን፤ይዘት በድግግሞሽ 2 በመቶኛ ሲሰላ 4.9% ከፍተኛ የተመዘገበ በድግግሞሽ 24 በመቶኛ 58.5% ጥሩ ደረጃ፣ በድግግሞሽ 15 በመቶኛ 36.6፣ ዝቅተኛ ሆኖ ከሌሎቹ ንኡሳን ክሂሎች የተሸለ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡የሀሳብ አደረጃጀት በመቶኛ 51.2% የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም 58.5%፣ሰዋሰዋዊ ትክክለኛነት 56.1%፣ስርአተ አጻጻፍ 65.9% በቅደም ተከተል በዝቅተኛ ደረጃ የተመዘሰገቡ መሆኑን በጥናቱ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው ጥቅል ውጤቱ እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው ዝቅተኛ ደርጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡በመጨረሻም በዚህ ጥናት ውስጥ የእጩ መምህራኑን የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የሚደረገው ጥረት ውጤታማ እንዲሆን አስተያየቶች ተሰንዝረዋል፡፡

ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

የጽህፈት ክሂል ትምህርት ዓላማ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው ሊያስተላልፉ የተፈለገውን መልእክት በጽሁፍ አቀናብረው መግለጽ ማስቻል ነው፡፡አንድ ጽሁፍ የተዋጣለት ነው ልንል የሚያስችለን፤የተፈለገውን መልእክት ለአንባቢው ግልጽ በሆነ መልኩ የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቆ ሲቀርብ ነው፡፡እንደ Sundem (2006፡99) ጥሩ/የተዋጣለት ጽሁፍ ማለት ይዘት፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት ምርጫ፣የዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣የሰዋስው አጠባበቅና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ጠብቆ የተፈለገውን ሀሳብ (መልእክት) በጽሁፍ ማስተላለፍ ሲችል ነው፡፡ይህ ክሂል ለአፈፊትም ሆነ ለኢ-አፈፊቶች በትምህርትና በልምምድ የሚያገኙት እንጂ እንደ ሌሎች ክሂሎች በሚኖሩበት ማህበረሰብ ለሚነገር ቋንቋ በመጋለጥ የሚለመድ አይደለም፡፡

ጽህፈትን አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ከነዚህም መካከል የጽሁፍን ውስብስብ ባህሪይ ሲያስረዱ Byrne (1988፡14) ጽህፈት የአዕምሮና የአካል እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት የአጻጻፍ ስልትን፣የጽሁፍ አወቃቀር ሥርዓትን፣የቃላት ምርጫን፣የሐሳብ ፍሰትንና ተያያዥነት ያላቸውን በርካታ ባህሪያትን ቅጽበታዊ በሆነ የመጻፍ ሂደት ውስጥ በመጠቀም የሚከናወን የአዕምሮ ሥራ ነው በማለት ገልጸውታል፡፡ይህንን ሀሳብ በማጠናከር የመጻፍ ክሂል የሀሳብ አደረጃጀትና የአንቀፅ አመሰራረት፣የዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም ለመጻፍ ክሂል ከሚያስፈልጉ ንዑሳን ክሂሎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ የክሂሉ ሌላኛው ባህሪው እየጻፉ መማርን ይጠይቃል በማለት (ማረው 2007፣135)፣(ተስፋዬ 1986:13) ፣(Grabe and Kplan 1996:6)፣(Hedge 1988:11) እና (Ur 1996፡26) በስፋት ገልጸውታል፡፡

የፅህፈት ችሎታን በተወሰነ ወቅት ተምረው የሚበቃ አይደለም፤በሂደት የሚዳብርና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እያየለ የሚሄድ በተጻፈ መጠን የሚያድግ ችሎታ ነው፡፡እየጻፉ መማር የሚጠይቅ ክሂል ነው፡፡ጽህፈት በትምህርት እንጂ እንደ ማዳመጥና መናገር በተጋልጦ ወይም በተፈጥሮ ሊገኝ የማይችል መሆኑን Grabe and Kplan (1996)

አፈፊትም ሆነ ኢ-አፈፊቶች ትምህርት ቤት ገብተው በትምህርትና በልምምድ ወይም ደጋግሞ በመጻፍ የሚዳብር መሆኑን (Hedge: 1988) እና (Ur 1996፡26) ገልጸውታል፡፡

እንደ Windowson (1990፡62) ጽህፈት በተግባራዊ መሳሪያነቱ የተገኘ የዕውቀት ማስተላለፊያ ብቻ ሳይሆን፣ሀሳብ አፍላቂ የክሂል ዘርፍ ከመሆኑም በላይ መረጃዎችን ወደ ዕውቀት ለውጦ መልዕክት ማቀበያ እና በትዕምርቶች ቀርፆ የማቆያ ስልት መሆኑን ገልጸውታል፡፡የጽህፈት ክሂል ታሪክን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለቀጣዩ ትውልድ ለማስተላለፍና ለማስፋፋት በየትኛውም ሊጻፍበት በሚችል ነገር ላይ ፊደላትን ተጠቅሞ ሀሳብን ማስፈር መሆኑን ከምሁራን ገለፃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ማንኛውም በአካልና በአዕምሮ ጤናማ የሆነ ሰው በአካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በመልመድ ሊናገር የሚችል ቢሆንም፤በቋንቋ እንዴት መጻፍ እንዳለበት ግን መማር አለበት በማለት (Nunan 1999፡36) የተነሳውን ሀሳብ አጠናክረውታል፡፡

ይሁን እንጂ ምሁራኑ የጥቅሙንና አስፈላጊነቱን ያህል ለክሂሉ ትኩረት እንዳልተሰጠው ገልጸውታል፡፡ከእነዚህም መካከል ተስፋዬ (1986፣9-10)"በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድረስት ሳንጽፍ ከትምህርት ቤት የምንወጣ ቁጥራችን ጥቂት አይደለም፡፡ በተለይ ከአስርና አስራ አምስት አመታት ወዲህ በተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣በትምህርት ክፍለ ጊዜ መብዛትና በመሳሰሉት ምክንያቶች እየተሳበበ የሚጻፈው ሳይታረም ይቀራል፤የተጻፈ ካልታረመ ስህተት ወይም ትክክል መሆኑና አለመሆኑ ስለማይታወቅ ካለመጻፍ ብዙም አይለይም"በማለት ለክሂሉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን አሳይተዋል፡፡በተጨማሪ ባዬ (2000፡xxvi)"ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየተመረቁ የሚወጡ ተማሪዎች ተራ ዘገባ ለማዘጋጀት ብቃት የላቸውም" ሲሉ ክሂሉ ያለበትን ሁኔታ አሳይተዋል፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ከቀደምት ጥናቶች መካከል በዋቢነት የሚጠቀሱ ክፍሌ (1986) የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡ኃይላይ (2011)ባደረጉት ጥናት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ሲያስረዱ ተማሪዎች ከጽሁፍ ፈተና ይልቅ አማራጭ መልሶችን ተጠቅመው ውጤት ማግኘት እንደሚፈልጉ ጠቁመዋል፡፡ በተመሳሳይ በአንደኛ ደረጃ፣በሁለተኛ ደረጃና

በኮሌጆች ያለውን የጽህፈት ክሂል ችግር ሌሎች ጥናቶች አመላክተዋል፤ከእነዚህም መካከል (ሙሉጌ 2003)፣(መሰረት 2003)፣(ተገኝ 2000)፣ (የአምላክስራ 2008)፣(ሁሴን 2009)እና (ተመስገን 2001) እነኝህ ጥናቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡በጥቅሉ ከዚህ በላይ የተነሱ ሀሳቦች ለጽህፈት ክሂል የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

1.2. አነሳሽ ምክንያት

ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነው የስራ አጋጣሚ ሲሆን፤ይህም አጥኝዋ በአርባምንጭ ከተማ በሚገኘው በሲቀላ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተደጋጋሚ ለልምምድ የሚወጡ የአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ እጩ መምህራን ያገኘችና በዚህ አጋጣሚ ያስተዋለችው እጩ መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ሲናገሩም ሆነ ሀሳባቸውን በጽሁፍ ሲገልጹ የሚቸገሩና፤ በተጨማሪም በተጨባጭ በደረጃው የሚማሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችግር እንዳለባቸው በማየቷ ይህንን የስራ አጋጣሚ መነሻ በማድረግ ችግሩን በጥናት ለማረጋገጥ ተነሳስታለች፡፡

ሌላኛው በጥናቱ ዳራ በስፋት ማየት እንደተሞከረው በምሁራኑ ዳሰሳ ክሂሉ ያለበት ደረጃ እንደግለሰብ፣እንደማህበረሰብ ብሎም እንደሀገር ሊያበረክት ከሚችለው ታሪካዊ፣ስነልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር አሁን ያለበት ደረጃ ደካማ መሆኑን ጥናቶች አመላክተዋል፡፡ለምሳሌ (ክፍሌ 1986) የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ እንደሌላቸው በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡(ኃይላይ 2011) በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችግር እንዳለባቸው አስቀምጠዋል፡፡ በተመሳሳይ (ሙሉጌታ 2003)፣(መሰርት 2003)፣ (ተገኝ 2000)፣ (የአምላክስራ 2008) ሌሎችም በጥናታቸው ተማሪዎች የተለያየ ዓይነት ስህተቶችን እንደሚፈፅሙ ለማወቅ ችለዋል፡፡ ስህተቶችም የበርካታ ተፅዕኖዎች ድምር ውጤት መሆናቸውን በዝርዝር አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በላይ በተጠቀሱ ጥናቶች በተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ችግር እንዳለባቸው ማየት ተችሏል፡፡ጥናቶቹ የሚያሳዩት የችግሩን ስፋትና አሳሳቢነት ሲሆን፤ሊሰራበትና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው አንደኛ ደረጃ በሚማሩ ህጻናት ለይ ቢሆን የተሸለ ውጤት ማግኘት

ይቻል ይሆናል በማለት በደረጃው ለማስተማር የሚመረቁ እጩ መምህራን ላይ ጥናት ቢደረግ በማለት ተነሳስታለች፡፡

አጢኝዋ ያየቻቸው ቀደምት ጥናቶች ችግር መኖሩን ከማሳየት ባለፈ ደረጃው ምን ያህል እንደሆነ አላዩትም፡፡ስለዚህ የስራ አጋጣሚ እና ከዚህ በላይ ያየቻቸው ጥናቶች መነሻ በማድረግ ለአንደኛ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ መምህርነት እየሰለጠኑ ያሉ ዕጩ መምህራን ሀሳባቸውን በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸውን መፈተሽና ያሉበትን ደረጃ ለማሳየት ወስናለች፡፡

1.3. የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ እጩ መምህራን ሀሳባቸውን በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታቸውን መፈተሽ ነው፡፡ይህንን መሰረት በማድረግ ዝርዝር አላማዎች እንደሚከተለው ተነድፈዋል፡፡እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ ያለውን፡-

ሀ/ የይዘት ስፋትና ጥልቀት መፈተሽ፤

ለ/ የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት መመርመር፤

ሐ/ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መፈተሽ፤

መ/ የሰዋስዋዊ ትክክለኛነት እና የአጻጻፍ ሥርዓታቸውን መፈተሽ፤

1.4. የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ፡-

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድረሰት ውስጥ፡-

ሀ/ ይዘቱን በጥልቀትና ስፋት ረገድ ግልጽና የተመጣጠነ አረፍተነገር መልእክት ማስተላለፍ ይችላሉ?

ለ/ የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት አለውን?

ሐ/ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል?

መ/ የሰዋስዋዊ ትክክለኛነት እና የአጻጻፍ ሥርአታቸው ምን ይመስላል?

1.6. የጥናቱ አስፈላጊነት (ጠቀሜታ)፡-

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

ሀ/ ይህ ጥናት የሚያስገኘው ጠቀሜታ ለአንደኛ ደረጃ አማርኛ መምህርነት የሚሰለጥኑ እጩ መምህራኑ እንዲሰለጥኑበት የሚዘጋጀው የማሰልጠኛ ወይም ማስተማርያ ሞጁል አዘጋጆች ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ለ/ አጥኝዋ በየደረጃው ለሚሰጠው የአማርኛ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል ወጥ የሆነ የደረጃ መለኪያ ያስፈልጋል ብላ ታምናለች፡፡ስለዚህ ደረጃ ማውጣት ለሚችሉና ለሚመለከታቸው አካላት መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ማለትም በአንደኛ ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣በመለስተኛ ደረጃ ለሚማሩ ተማሪዎች፣ከተለያዩ ተቋማት ለሚመረቁ ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ብቃት ደረጃ ሊወሰንና ሊቀመጥ ያስፈልጋልና በዚህ ጉዳይ ምርምር ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

ሐ/ ለተደራሽነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ለዲላ ዩኒቨረሲቲ ይቀርባል፤ቀጠሎም ጥናቱ ለተካሄደበት ለአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ይሰጣል፤በተጨማሪም በጥናትና ምርምር ድህረ ገጾች ላይ እንዲለቀቅ ጥረት ይደረጋል፡፡

1.7. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚካሄደው ቦንጋ፣ዲላ፣አርባምንጭ እና ሆሳእና ከ4 በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት ከሚገኙ የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች መካከል አንዱ በሆነው በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ነው፡፡ምክንያቱም አጥኛዋ በምትኖርበት አቅራቢያ የሚገኝ በመሆኑ አስፈላጊውን መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ አይሆንም፤በተጨማሪም ገንዘብ፣ጊዜና ጉልበት ይቆጥባል፡፡የተመረጡት ተጠኝዎች በ2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በኮሌጁ በሁለተኛ እርከን (ክላስተር) ዲፕሎማ መረሃ-ግብር ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ተመራቂ እጩ መምህራን ናቸው፡፡ሀሳባቸውን በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታ መፈተሽ ሲሆን በሚጽፏቸው ዐረፍተ ነገሮችና ጽሁፎች /ድርሰቶች/ ውስጥ የይዘት ስፋትና ጥልቀት፣ የሀሳብ አወቃቀር፣የቃላት ምርጫና አጠቃቀም፣ የሰዋስው

ህግጋት አጠባበቃቸውንና የአጻጻፍ ሥርዓታቸውን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ከተቀመጡ ነጥቦች ውጪ ይህ ጥናት አይመለከትም፡፡

1.8. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ከጊዜና ከትግበራ ሂደቶች አንጻር ውስንነቶች አሉት፡፡መረጃ አሰባሰብ ላይ በኮሮና ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች መዘጋታቸው፤ቢከፈቱም የተሰጣቸው የትምህርት ጊዜ አጭር በመሆኑ በቂ ጊዜ ወስዶ መረጃ ለመሰብሰብ አሰቸጋሪ መሆኑ፤በተጨማሪም መረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጁ 10 ርዕሶች ተገቢነታቸውን በኮሌጁ ሶስት መምህራን ተገምግመው ይሁንታን ካገኙ በኋላ በአቻ ትምህርት ቤት በተመሳሳይ ዕጩ መምህራን ላይ ሙከራ መደረግ ሲኖርበት፡፡ነገር ግን በወረርሽኙ ምክንያት ተግባራዊ አለመደረጉ ውጤቱ ላይ ተጽኖ አሳድሮ ሊሆን ይችላል፡፡

ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን

2.1 የጽህፈት ክሂል

ጽሁፍ የሰው ልጆች ሀሳብ ለሀሳብ የሚለዋወጡበትና መረጃዎችን ሰንዶ ከትውልድ ትውልድ ማስተላለፊያ መንገድ ሲሆን፤መጻፍ በዘፈቀደ ፊደላትን ወይም ቃላትን በወረቀት ላይ ወይም ሊጻፍበት በሚችል ነገር ላይ መጻፍ ብቻ ተደርጎ ሊውሰድ አይገባም።ምክንያቱም ጽሁፍን ለማከናወን ቢያንስ ስለሚጻፈው ጉዳይ ማሰብ፣ያሰቡትን ማርቀቅ፣መከለስና እንደገና መልሶ መጻፍ። እነዚህን ሦስት ደረጃዎችን ማለፍ አለበት።

በርካታ ምሁራን ጽህፈትን አስመልክተው የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል።ከነዚህም መካከል Byrne (1991፡1) ጽህፈት ማለት በንግግር ጊዜ የምንጠቀምባቸውን ድምፆችን ሊወኪሉ የሚችሉ ትዕምርቶች ቅንብር ነው።ይህ ማለት ሆሄያትና ምልክቶች ሲደረደሩ ሁሉ በተስማማበት፣ትርጉም ባለው መልኩ ቃላትን፣ሀረጋትን፣አረፍተ ነገሮችን መመስረት በሚያስችል መልኩ መሆን አለበት በማለት ገልጸዋል።Nunan (1999:273) ስለጽሁፍ ምንነት ሲያስረዱ ድምጾች በተሰጣቸው ትእምርቶች አማካይነት አንባቢ ሊረዳ በሚችለው መንገድ ሀሳብን በጽሁፍ መግለጽ ማለት ነው። በተጨማሪ (Zamel 1983:165) ሀሳብን ለአንባቢ ግልጽ በሆነ መልኩ ማፍለቅ፣ማደራጀትና የመግለጽ ክዋኔ መሆኑን አስረድተዋል።

ዳዊት (2008) በጥናታቸው Wallaca እና ሌሎችን (2004) ጠቅሰው የጽህፈት ምንነትን ሲያስረዱ ጽህፈት ከሰው ልጆች የተግባራዊ ሂደቶች መከወኛ መሳሪያ ውስጥ አንዱ ሲሆን በቋንቋ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተቀርፆ የሚገኝ ነገር ግን በማንኛውም የትምህርት ዓይነት ውስጥ ጉልህ ሚና ያለው የቋንቋ ክሂል ዓይነት መሆኑን ገልፀዋል። ጽህፈት አቻ የሌለው (Excellent way) ፣ጠንካራ አቅም ያለው (Writing is powerful) እና በሌሎች መግባቢያ መንገዶች ሊረታ የማይችል ሀሳብን በነፃነት መግለጫ መንገድ ነው በማለት (https://pixelgrade.com 2019:1) በዚህ ድህረገጽ ተገልቷል።

በተጨማሪ እንደ Byrne (1991፡14) እና Nunan(1989:36) የጽህፈትን ክሂል ውስብስብ ባህሪይ ሲያስረዱ ጽህፈት የአካልና የአዕምሮ እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት የአጻጻፍ ስልትን፣የአወቃቀር ሥርዓትን፣የቃላት ምርጫን፣የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት ያለው

ባህሪያቱን በአንድ ጊዜ የሚያከናውን ውስብስብ የአዕምሮ ሥራ ነው በማለት ገልጸውታል ::

በአጠቃላይ ጽህፈት ሀሳብን (መልእክትን) በጽሁፍ ለሌላ ወገን፤ሊጻፍበት በሚችል ነገር ላይ በመጻፍ ማስተላልፍ ነው።ማስተላለፍ ስንል ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መልኩ መሆን አለበት። ስሜት ፈጥሮ መልእክት ማስተላለፍ የሚቻለው ይዘት፣የቋንቋውን ህግ(ሰዋስው)፣ስርዓተ-ነጥብ፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት ያለውና በአግባቡ የተዋቀረ፤ለአንባቢ የማይጎረብጥ ሆኖ ሊጻፍ ይገባል።ሌላው የጽሁፉ ክሂል በአከባቢው ከሚኖሩ ማህበረሰብ ጋር አብሮ በመኖር ወይም ለቋንቋ በመጋለጥ የሚለመድ አለመሆኑ፣በዕኩል ሰአት የአካልና የአምሮ እንቅስቃሴ የሚፈልግ መሆኑ ውስብስብ ባህሪ ያለው መሆኑን ከምሁራን ገለጻ መረዳት የቻላል።

2.2 ጽህፈትን አስቸጋሪ የሚያደርጉት

የጽሁፍ ክሂልን አስቸ ጋሪ የሚያደርገው ውስብስብና ረቂቅ ባህሪያት ያሉት ክሂል በመሆኑ ነው። እንደ Byrne (1991) የጽፈትን ክሂል አስቸጋሪ የሚያደርጉ ሦስት ዋና ዋና ተላውጦዎች እንዳሉ አስረድተዋል።እነዚህም የስነ-ልቦና፣የስነ-ልሳን፣የስነ-አዕምሯዊ ችግሮች ናቸው።እነዚህም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርበዋል።

ሀ/ የስነልቦና ችግር፡- Byren(1991፡14) በተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ተላውጦዎች መካከል የስነልቦና ችግር አንዱ ነው በማለት ገልፀዋል።የስነ ልቦና ችግር በጽህፈት ጊዜ ሀሳብን የማፍለቅ ሂደት ሲሆን፤በሌላ በኩል የጽሁፍ ክሂልን ያለውጫዊ መስተጋብር በራስ ስሜት ብቻ ለመከወን ማሰብ በራሱ ጽህፈትን አስቸጋሪ ያደርገዋል። ጸሀፊውና አንባቢው ፊትለፊት ተገናኝተው የሚከወን መስተጋብር አለመሆኑ በጻፊ ላይ ጭንቀት ይፈጥራል፤ በሚጽፈው ጽሁፍ ውስጥ ስህተት እፈጽም ይሆን? የመጽፈው ጽሁፍ ተነባቢነትስ ይኖረውይሆን? እያለ ስሚያስብ የስነልቦና ችግር ሊገጥመው ይችላል። በንግግር ጊዜ ግን በሚደርግ መስተጋብር ተናጋሪው ከአድማጩ ወዲያው ግብረ-መልስ ስለሚያገኝ መልእክቱን አስተካክሎ ማስተላለፍ ይቻላል።

ለ/ የስነ ልሳን ችግር ፡-በጽሁፍ አማከኝነት መልእክት በተገቢው ማስተላለፍ ከተፈለገ የቋንቋውን ህግ/ውስጣዊ ባህሪ ማወቅ አስፈላጊ ነው።እንደ Byren (1988፡4) በንግግር ጊዜ የሚንጠቀምባቸው ድምፀቶች ወይም የምናወጣቸው ድምፆች በጽሁፍ ጊዜ ግን

የማንጠቀምባቸውን ለማካካስ ጸሐፊው ትክክለኛውን የጽህፈት ቅርፅና ተገቢውን አያያዣ ቃላት በመጠቀም ጽሑፉ ራሱን በራሱ እንድገልፅ ማስቻል አለበት፡፡በተመሳሳይ (Hedge 1988፡5) በጽሁፍ ውስጥ በንግግር ጊዜ ያሉትን ድምፆች ለማካካስ ዐረፍተነገሮችን በሚገባ በማደራጀት በጥንቃቄ የተመረጡ ቃላትና ትክክለኛ ሰዋስው መጠቀም አለበት፡፡ስለዚህ የሰዋስው፣የሥርዓተ ነጥብ፣የዐረፍተ ነገር ቅርፅና የቃላት ምርጫ ዋናዎቹ የጽሁፍ ክሂልን ባህሪ ውስብስብ የሚያደርጉ ናቸው በማለት ገልፀውታል፡፡

ሐ/ የስነአምሮአዊ ችግር፡-Byren (1998፡16) ጽህፈት በትዕምርቶች የመወከል ሂደት ብቻ ሳይሆን የአዕምሮና የአካል እንቅስቃሴዎችን በማቀናጀት የጽሁፉ ይዘት፣ሥርዓተ ነጥብ፣የአፃፃፍ ስልት፣ የአወቃቀር ስርዓት፣የቃላት ምርጫ፣የሀሳብ ፍሰትና የመሳሰሉትን በርካታ ባህርያት የአዕምሮ ሥራ መሆናቸው ጽሁፍን ከባድና ውስብስብ እንዲሆን ያደርጉታል በማለት ገልጸውታል፡፡

መ/ ምጋቤምላሽ፡- ምጋቤምላሽ አንዱ የተማሪዎችን የፅህፈት ክሂል ለማጎልበት አጋዥና በመማር መስተማር ሂደት ውስጥ ያለው ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡እንደ Zamel(1985:79) ገለጻ የመምህራን ምጋቤምላሽ በተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው ከፍተኛ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል ሲሉ፤በተመሳሳይ(Byrne1988:29)ሀሳቡን አጠናክረውታል፡፡ዳዊት(2008) ባደረጉት ጥናት ሲገልፁ የተማሪዎች የጽሁፍ ክሂል ዕድገት ላይ ጉልህ ሚና እንዳለው አረጋግጠዋል፡፡ በተጨማሪም የሽሐረግ (2010) ምጋቤምላሽ በተማሪዎች የድርሰት የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ማየት ችለዋል፡፡እንደ Caroline (2005፡105) የምጋቤምላሽ ጠቀሜታ የሚያካትቷቸው የተማሪዎችን የጽሁፍ ክሂል እንዲዳብር ያደርጋል፤ ተማሪዎቹ በቀጣይ ጽሁፋቸውን እንዴት መጻፍ እንዳለባቸው ያመላክታል፤መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ጽሁፉ ጠንካራ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ያሣያል፡፡

በአጠቃላይ ምጋቤምላሽ የተማሪዎችን የጽሁፍ ችሎታ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችልና መምህራን ተገቢውን የግብረ-መልስ ዓይነት በተገቢው ቦታና ሁኔታ በመጠቀም ምጋቤምላሽ ባለመስጠቱ ምክንያት የሚመጣውን የጽሁፍ አስቸጋርነትን መቅረፍ ይቻላል፡፡

2.3 የተዋጣለት/ጥሩ ጽሁፍ

አንድን ጽሁፍ የተዋጣለት/ጥሩ ሊያስብል የሚችለው የተለያዩ መስፈርቶችን አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡እንደ Robert(1990) አገላለጽ በሶስት ይከፍላቸዋል እነዚህም ግልጸኝነት (clarity)፣የሀሳብ ተያያዥነት (coherence)እና ባነሳው ሀሳብ ላይ ትኩረት (focus) መደረግ እንዳለበት አሳይተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሌሎች ምሁራንም ይህንን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል ከእነዚህም መካከል Sunde(2006) ደረጀ(1996) አማረ(1986) ሲሆኑ ያነሱአቸው ነጥቦች ይዘት፣የሃሳብ አደረጃጀት፣ሰዋስው፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ ስርአተ አጻጻፍ ናቸው፡፡በተመሳሳይ Reid (1993) የተዋጣለት ፅሁፍ ማለት ለማስተላለፍ የተፈለገው ሀሳብ የተገለፀበትና የተጻፉ ዐረፍተ ነገሮች በበቂ ሁኔታ የመግለፅ አቅም ያላቸው ሲሆኑ ነው በማለት ገልጸዋል፡፡እነዚህን እና ሌሎችንም ከዚህ ቀጥሎ በዝርዝር ይቀረባሉ፡-

ሀ/ ይዘት (Content)፡- አንድ ጽሁፍ ትኩረት አድርጎ የሚያውጠነጥንበት ሐሳብ ሲሆን፤አንባቢው ምን እንድያውቅ ተፈለገ? ምን ዓይነት ሀሳብ እንድይዝ /እንድያስተላልፍ/ ተፈለገ? የሚሉትን አበይት ጉዳዮችን ይይዛል፡፡በተጨማሪም በአንድ የተዋጣለት ጽሁፍ ውስጥ የተሟላ እውቀት የያዘ እና በጽሁፉ ስለተነሱ ርዕሰ ጉዳዮች በደንብ የሚያበራራ መሆኑን sundem (2006፡101) አስረድተዋል፡፡

ለ/ የጽሁፍ አወቃቀር (Organaization)፡- የጥሩ ጽሁፍ አዋቀር የሚባለው ተገቢው ዐረፍተ ነገር በተገቢው ቦታ በማድረግ፣የአረፍተ ነገሮቹ አሰላለፍ አብይና ንኡስ ሀሳቦች በአግባቡ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ሲሰደሩ ሀሳብን በሚገባ ለማስተላለፍ ከመቻሉም በላይ የአንባቢውን ቀልብ የመያዝ (የመቆጣጠር) አቅም ይኖረዋል፡፡እንደ Rrbert(1990) በግልጽ የተደራጀ የሀሳብ ፍሰት አረፍተነገሮች ከአረፍተነገሮች ጋር እንዲሁም አንጾች ከአንቀጾች ጋር የጠበቀ የሀሳብ ተያያዥነት ሊኖራቸው እንደሚገባ ሲያስረዱ ሂደቱንም ርዕስ መምረጥ(title)፣በመጀመሪያው ክፍል መግቢያ መጻፍ (introduction)፣በዋናው የጽሁፉ አካል ማብራርያ መጻፍ(main body) እና በስተ መጨረሻ ስለተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ማጠቃለያ መስጠት (conclusion) እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ሐ/ የቃላት ምርጫ፡-ሀሳብን በጽሁፍ አቀናብሮ ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው ቃላት ወሳኝ ናቸው፡፡ እንደ አማረ (1986፡4) ‹‹ቃላት የደራሲ ቀኝ እጆች ናቸው፡፡›› በማለት ቃላት

ሀሳበን ለመግለጽ ምንያህል ቦታ እንዳላቸው በአገላለጻቸውም ጭምር አስረድተዋል፡፡ የምንጠቀምባቸው ቃላት አሻሚት የሌላቸው፣ለአንባቢ በቀላሉ ሊረዳው የማይከብዱ፣ገላጭ የሆኑ፣ተገቢውን ቃል በተገቢው ቦታ በመጠቀም በአንባቢው አዕምሮ ውስጥ ምስል ከሳች የሆነ መልዕክት /ሀሳብ/ ሊሸከም እንዲሁም ሊያስተላልፍ የሚችል ቃል በመጠቀም ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት በአግባቡ ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

መ/ ሰዋስው አጠባበቅ (Grammer)፡-ጥሩ የዐረፍተነገር አወቃቀር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ፣ የጾታ፣የጊዜ፣የመደብና የቁጥር ስምምነትን ጠብቆ በንባብ ጊዜ የአንባቢውን ሳይዝ፣ ሳያቋርጥ፣ ሳያደናቅፍ ፍሰቱ ለአንባቢ የሚጥም/ስሜት የሚገዛ ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ/ ስርአተ-አጻጻፍ (mechanics):- ከፊደላት አጣጣል ፣ሳድስና ሳልስ አጠቃቀም፣የምንጽፍበት ወረቀት ህዳግችን እንዴት ነው የምንተቀመው፣የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ተገቢነቱን ከተጠበቀ፤ የሚጻፈው ጽሁፍ ውበት እንዲኖረው በማድረግ የአንባቢውን ቀልብ በመሳብ ተነሳሽነትን ይፈጥራል፡፡

ረ/ ስርአተ-ነጥብ፡- የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም፤በምንጽፈው ጽሁፍ ውስጥ የሚሰጠው የትርጉም ለውጥ ቀላል አይደለም፡፡ስርአተ ነጥብ በጽሁፍ ውስጥ የጽሁፉን ሀሳብ ለማግኘት የድምጽ ወይም ለመረዳት ከቃላት በተጨማሪ ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ደረጀ (1996፣45) አስረድተዋል፡፡ስለዚህ ተገቢውን ስረአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ በመጠቀም ማስተላለፍ የተፈለገውን መልእክት በትክክል ማስተላለፍ ይቻላል፡፡

ሰ/ የዐረፍተ ነገር አገላለፅ /Sentnce fluency/- የጥሩ ዐረፍተ ነገር አወቃቀር የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ፣የጾታ፣የጊዜ፣የመደብና የቁጥር ስምምነትን ጠብቆ በንባብ ጊዜ የአንባቢውን ሳይዝ፣ ሳያቋርጥ፣ሳያደናቅፍ ፍሰቱ ለአንባቢ የሚጥም/ስሜት የሚገዛ ሊሆን ይገባል በማለት(sundem 2006፡101) ገልፀውታል፡፡

ሸ/ የአጻጻፍ ስልት (Voice):- የአፃፃፍ ስልቱ የጸሀፊውን ማንነት ይገልፃል፤በሌላ በኩል አንባቢው ማነው?የሚለውን ያገናዘበ ነው፡፡የአንድ ጽሁፍ አጻጻፍ ለሁሉም አንባቢ ሊሆን አይችልም፡፡ የሚጻፈው ጽሁፍ ስለንግድ፣ቀልድ፣ትምህርታዊ ወይም ጥናታዊ ጽሁፍ ወዘተ… የራሳቸው የሆነ አጻጻፍ ስልት አላቸው፡፡ለምሳሌ፡-ለነጋዴ የሚጻፍ ጽሁፍ ዓይነትና ለህፃናት የሚጻፍ ጽሁፍ ወይም ጥናታዊ ጽሁፍ ብንወስድ የየራሳቸው አጻጻፍና

አንባቢ አላቸው በማለት sundem (2006) ገልተውታል፡፡በተመሳሳይ የምንጽፋቸው ጽሁፎች የአንባቢውን ማንነት መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን(ማረው 2005፣2) ገልጸው አስረድተዋል፡፡ስለዚህ ከምንጽፈው ጽሁፍ ጀርባ አንባቢው ማነው? የሚለውን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

2.4 የጽሁፍ ክሂል መማር ጠቀሜታ

የጽሁፍ ክሂል መማር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡የጽሁፍ ክሂልን መማር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ለማዳበር ሲሆን፡፡የምንፅፈው ጽሁፍ ለማንነው? ለምንድ ነው የምንጽፈው? የጽሁፉ ይዘት ምን ይመስላል? ሀሳቡን በአገባቡ ማደራጀትን፣የምንጠቀማቸው ቃላት ለአንባቢ ግልጽና በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችሉ መሆናቸውን እና የመሳሰሉትን አሟልተን የተስተካከለ የአጻጻፍ ቅርፅ የያዘ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ብቃት እንዲያድግ ያግዘናል በማለት (Heaton 1991:134) (Byren 1991:6) እና (Lazaro 1996 :91) አስረድተዋል፡፡በተጨማሪም የጽሁፍ ክሂል መማር በትምህርት ቤትም ሆነ በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ፋይዳ እንዲህ ያብራሩታል፡፡

ሀ/ ለፈተና፡-ዋናው ጠቀሜታ ሲሆን የፈተናው ዓይነትም ድርሰት መፃፍ፣የጽሁፍ ፈተናዎች፣ የተለያዩ ላቦራቶሪ (ቤተ ሙከራዎች) ሪፖርቶች፣ወዘተ…ሲሆን፤ትኩረቱን የሚያደርገው በይዘትና በአጻጻፍ ሥርዓት ላይ ነው፡፡ይህም ማለት የቋንቋ አጠቃቀም፣የአጻጻፍ ቅርፅ፣የማነፃፀር ችሎታ፣ ሰዋስውና የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ላይ ያተኩራል፡፡

ለ/ ለትምህርት፡- ሁለተኛ የጽሁፍ ክሂል ጠቀሜታው በአጠቃላይ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት፣ የማ ሰላሰልና የፈጠራ ችሎታቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንድያድግ ያግዛል፡፡

ሐ/ ለተግባቦት፡- ከመግባቢያ መንገዶች አንዱ ሲሆን በምሁራን የሚደረገው የዕውቀት ሽግግርና የሀሳብ ምዘናዎች ላይ ቀዳሚ መንገድ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ተማሪዎች በሚማሩት ሙያ ዘርፍ የአጻጻፍ ዘዴ ተከትለው ጽሁፎችን እንዲ ጽፉ ያግዛቸዋል፡፡በሌላ አገላለጽ ሀሳብ ማስተላለፍና ተግባቦት ለመመስረት ያግዛል፡፡

2.5 የጽሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች እና መልመጃ አዘገጃጀት

2.5.1 የጽሁፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

ከዚህ ከፍ ብሎ የጽሁፍ አስፈለጊነትን በአጭሩ ለማየት ተሞክሯል፡፡ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው የጽሁፍ ክሂል አቀራረብ ነው፡፡የጽሁፍ ክሂል ትምህርት በርካታ አቀራረቦች ቢኖሩትም የሚዘወተሩት አቀራረቦች ሁለት ናቸው፡፡እንደ Lazaro (1996፡92) ውጤት ተኮር አቀራረብ እና ሂደት ተኮር አቀራረብ ናቸው፡፡እነሱንም በዝርዝር ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ሀ/ ውጤት ተኮር አቀራረብ፡- እንደ Coffin,Curry እና ሌሎች (2005፡9) ውጤት ተኮር አቀራረብ የሚያተኩረው የሚጻፈው ጽሁፍ ወይም ድርሰት ውጤት ላይ መሰረት ያደረገ ሲሆን ተመራጭ የሚሆነው በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላሉ ተማሪዎች ነው፡፡ይህ አቀራረብ የሰዋስው ትክክለኛነት ላይ ያተኩራል፡፡በተመሳሳይ (Raimes 1983:6) ይህን አቀራረብ ተማሪዎች በራሳቸው ስህተታቸውን እንዲያርሙ እድል አይሰጥም፣ሲጽፉ ስህተትን አስወግደው የሰዋስው ህግን በመከተል ትክክለኛውን የዐረፍተ ነገር አወቃቀር ጠብቀው መጻፍ እንዳለባቸው ያስቀምጣል (Hedge 1988:8)ይህንኑ ሀሳብ አጠናክረዋል፡፡

ለ/ሂደት ተኮር አቀራረብ፡- ሂደት ተኮር አቀራረብ የተለያዩ ደረጃዎችን የጠበቀና ደጋግሞ በመጻፍ የተሻለ ጽሁፍን ማግኘት እንደሚያስችል ያምናል፡፡ይህ ሂደት ተኮር አቀራረብ በተለያዩ ምሁራን ተመራጭ የሆነ ጽህፈትን ማስተማሪያ መንገድ ነው፡፡ እንደ Coffin,Curry እና ሌሎች (2005፡34)፣ Alderson & Bachman (2002፡22-36)፣Sundem (2007፡41-48) እና Kroll (1990፡15) ሂደታዊ ጽሁፍ ማለት የተጻፈን ጽሁፍ ደጋግሞ መጻፍ ማለት ሳይሆን ከአዕምሮ አፍልቆ የተለያዩ ደረጃዎችን አልፎ የሚገኝ ውጤት ነው፡፡ በተጨማሪም የጽሁፍ ስራ የአንድ ጊዜ ተግባር አይደለም ሲሉ ጥራት ያለው ጽሁፍ ለመጻፍ ማሰብ፣ማርቀቅ፣እንደገና ማሰብና ማርቀቅ፣ትኩረቱን መለየት፣መከለስ፣ማስተካከልና ለመጨረሻ ጊዜ አጣርቶ ማንበብን ይጠይቃል በማለት(ማረው 2005፡52) ገልጸዋል፡፡ሂደት ተኮር አቀራረብን አስመልክቶ ከላይ ከተጠቀሱ ምሁራን መካከል ለአብነት ሂደቱን ሊገልፅ የሚችል ሥዕል ከCoffin,Curry እና ሌሎች (2005፡34) ተወስዷል፡፡



ስዕል. 1 **ሂደታዊ ጽሁፍ እንደ** Coffin, Curry **እና ሌሎች** (2005፡34)

2.5.2. **የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች**

እንደ Lazaro (1996፡95) መምህሩ ለፅህፈት ክሂል መልመጃ ዕቅድ ሲያቅድ የተማሪዎችን ደረጃ የመጠነ እና ከአቅም በላይ ወይም በታች መሆን የለበትም፡፡በዝቅተኛው የትምህርት ደረጃ በዐረፍተ ነገር ደረጃ የተገደበና ቀስ በቀስ እያደገ አንቀፅና ከዚያም በላይ መሄድ ወይም ከፍ ማለት ይችላል፡፡ሌላው ድግሞ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ልቅ ጽሁፍ እንድፅፉ በማድረግ መምህራን ድጋፍ ያደርጉላቸዋል፡፡

የተማሪዎችን የፅሁፍ ክሂል ለማሳደግ የተለያዩ ሦስት መልመጃ ዓይነቶችን መጠቀም እንደሚቻል (Sundem 2007፡123) እና (Lazaro 1996፡95) በተጨማሪ አብራርቷል፡፡

ሀ/ ግድብ /ውስን መልመጃ (Controlled writing activity)-ይህ ጽህፈት መልመጃ የተማሪዎችን አመንጪ /ፈጠሪ/ ሆነው አናገኛቸውም ምክንያቱም የተሰጣቸውን ፅሁፍ እንዲገልብጡ ባዶ ቦታዎችን እንድሞሉ፣የተዘበራረቁ ዐረፍተ ነገሮችንና ቃላቶችን

እንድያስተካክሉና መሰል ሥራዎችን እንድሠሩ የሚሰጥና ለጀማሪ ተማሪዎች የሚቀርብ የጽሁፍ መልመጃ ነው፡፡በዚህ ጊዜ ስህተት አይጠበቅም፡፡

ለ/ ፍንጭ ሰጪ መልመጃ (Guided writing Activity)

ፍንጭ ሰጪ መልመጃ ከውስን መልመጃ ይልቅ ተማሪዎች አመንጪ የሚሆኑበትና በተወሰነ ደረጃ ያላለቁ ጽሁፎችን እንድጨርሱ፣ቢጋሮችን ተጠቅሞ ሀሳብ እንድያጠናክሩ እና ባዶ በታዎችን እንድሞሉ ስለሚያደርግ የተሻለ ነው፡፡Alberto ይህንን በሁለት መንገድ ይመለከቱታል፡፡እነሱም ውጤት ተኮር እና ሂደታዊ ናቸው፡፡

ውጤት ተኮር አቀራረብ፡- በሚሆንበት ጊዜ ጽሁፍ እንድያነቡ በማድረግ ዋናውን ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንዲጽፉ፣ማጠቃለያ እንዲጽፉ፣ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት የእረፍት ጊዜህን እንዴት አሳለፍክ? የሚሉና የመሳሰሉ ፍንጭ ሰጪ ጥያቄዎችን በመስጠት እየጻፉ እንዲለማመዱ የሚሰጥ የመልመጃ አይነት ነው፡፡
ሂደት ተኮር አቀራረብ፡- በሚሆንበት ጊዜ መምህሩ ርዕስ ወይም ቢጋራ በማዘጋጀት ተማሪዎችን በቡድን ወይም በግል እንድጽፉ ያደርጋቸዋል፡፡ተማሪዎችም እያንዳንዱን ሂደት ጠብቀው በተሰጣቸው ርዕስ ዙሪያ ያለምንም መረበሽ የተሰጣቸውን ሰዓት ጠብቀው ይጽፋሉ፡፡

ሐ/ ልቅ/ነጻ/ የፅሁፍ መልመጃ (Free writing) - ይህ የመልመጃ ዓይነት ለተማሪዎች ሙሉ ነፃነት ይሰጣቸዋል፡፡ተማሪዎችም የጽህፈት ክሂላቸውን እንድያሳድጉ ያግዛቸዋል፡፡ቀድሞ ካየናቸው ሁለቱ መልመጃ ዓይነቶች ይለያል የአፍልቆት አቅማቸውን ከፍ ያለ እንዲሆን ያግዛል በማለት አስረድተዋል፡፡ይህ የመልመጃ አይነት ለተማሪዎች ሰፊ ነጻነት ስለሚሰጣቸው፤በማነቃቃት ያላቸውን የጽሁፍ ተነሳሽነታቸውን ከፍ እንዲል ያደርጋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው የተለያዩ በርካታ የመልመጃ አቀራረቦች መኖራቸውን ሲሆን ከአተገባበር ረገድ መታየት ያለበት ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ እና ከትምህርቱ ይዘት ከግምት ውስጥ በማስገባት መርጦ መጠቀም የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ከፍ በማድረግ ውጤታማ የመማር ማስተማር ሁኔታ መፍጠር እንደሚቻል ነው፡፡

2.6 የመጻፍ ክሂል መመዘኛዎች

የተዋጣለት ጽሁፍ ማለት ሊያስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ/መልዕክት በትክክል በተፈለገው መንገድ ስሜት ፈጥሮ ለአንባቢያን ማስተላለፍ መቻል ነው፡፡አንድን ጽሁፍ የተዋጣለት ጥሩ ጽሁፍ ነው ሊያስብሉ የሚችሉ መመዘኛዎች(መስፈርቶች) መፈተሽ ይኖርባቸዋል፡፡እንደ Alderson and Bachman (2002:116) Sundem (2006፡99) Brenda (2019:1-6) እና Murray and Anna አንድን ጽሁፍ የተዋጣለት ወይም ጥሩ ጽሁፍ ነው ማለት አስቸጋሪ ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡ነገር ግን ጥሩ ጽሁፍ እንደ አንባቢው፣ እንደ ጸሐፊው እና እንደ ጽሁፉ ይዘት ሊጻፍ ይችላል፡፡ለምሳሌ ጥናታዊ ጽሁፍ፣የንግድ ስራ ማስታወቂያ፣ቀልዶች ሌሎችንም ማየት ይቻላል፡፡ጥሩ የሚባለው ጽሁፍ በረካታ አላባውያን አሉት፤ያነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ምንያህል የተስተካከለ የዐረፍተ ነገር አወቃቀር፣የሀሳብ አንድነት፣ካለው የሀሳብ ፍሰት፣ካካተተው ይዘት፣ከቃላት ምርጫና አጠቃቀም፣ከሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አኳያ እንድሁም ከሰዋስው አንፃር ከጸሐፊው የአጻጻፍ ስልት ሊገመገም ወይም ሊፈተሽና ደረጃ ሊሰጠው ይችላል በማለት ገልፀውታል፡፡

ምሁራን ለተለያዩ አላማዎች የተለያዩ መመዘኛ መስፈርቶች ይጠቀማሉ፡፡የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ መስፈርቶች ሲመዝኑ ይታያሉ፡፡ይህ ማለት ወጥ የሆነ መመዘኛ መስፈርት አለመኖሩን ያሳያል፡፡እንደ Sundem (2006፡68) አገላለፅ የጥሩ ፅሑፍ (Good writing) መመዘኛ መስፈርቶች ወይም ተላውጦች የአጻጻፍ ስልት፣የሀሳብ አወቃቀር፣ የዐረፍተ ነገር ፍሰት፣የቃላት ምርጫ፣ርዕሰ ጉዳይ (Ideas)፣የሥርዓተ ነጥብ፣የሰዋስው፣የጽሁፉ ቅርፅ እና አንዳንድ ጊዜ አቅርቦት (Presentation) እነዚህን ነጥቦች በመጠቀም ከ1-4 /1-5/1-6 ሊመዘን የተፈለገውን የጽሁፍ ዓላማ መሰረት በማድረግ መመዘንና ደረጃ መስጠት እንደሚቻል ገልፀዋል፡፡

Alderson and Bachman መስፈርት አድርገው የተነሱት ይዘት (content)፣አደረጃጀት (organization)፣ቃላት (vocabulary)፣የቋንቋው አጠቃቀም/ሰዋስው (language use) እና ሥር-አተአጻጻፍ (mechanics)ናቸው፡፡ከእነዚህ አለባውያን አንጻር ሊመዘንና ደርጃ መስጠት እንደሚቻል ምሁራኑ አብራርተዋ፡፡በዚህም ጥናት የእጩ መምህራኑን የጽሁፍ ችሎታ ያለበትን ደረጃ ለመመዘን ኃይላይ (2011) በጥናታቸው ከፋሪሲ (2003) እና ከማገረው (2005) አሻሽለው የተጠቀሟቸው መስፈርቶች ተግባር ላይ ውሏል፡፡ይህም

ይዘት፣የሀሳብ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ሰዋስው አጠባበቅ እና ስርአተ አጻጻፍ የተከተሉ ናቸው፡፡

2.7 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኝዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ ስትነሳ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል ብላ ያሰበቻቸውን ጥናቶች ለማግኘት ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመሄድ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶችን ማየት ሞክራለች፡፡ ካገኘቻቸው ጥናቶች መካከል፡-

ክፍሌ(1986) የዚህ ጥናት ዓላማ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ አቀናብረው ለመግለፅ ያላቸውን ችሎታ ማጥናት ነው፡፡በጥናቱም የተገኘው ውጤት ተጠኝ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡ተጠኝ ተማሪዎቹ ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ወይም መልዕክት በትክክል የሚገልፁበትን ቃላት በትክክለኛ አሰካክ ጠብቀው የመፃፍና ሀሳብ አቀናብረው የመግለፅ ችሎታቸው አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡በተለይ አንቀፅ ለመጻፍ ያላቸው ልምድ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይጠቁማል፡፡ ይህ ጥናት በአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ እና የቆየ ጥናት በመሆኑ በዚያን ጊዜ የነበረው ሥርዓተ ትምህርት፣መረሀ-ትምህርትና የመጽሐፍት ዝግጅት ሰፊ ልዩነት ያለው በመሆኑ አሁን ባለው ሁኔታ ጥናት ማጥናት አስፈላጊ ሆኖ አግኝታለች፡፡

ሁሴን (2009) ባደረጉት ጥናት ይዞ የተነሳው አቢይ ዓላማ በጋምቤላ መምህራንና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአማሪኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የሚማሩ የሁለተኛ አመት ተማሪዎች አፈፈትና ኢ- አፈፈቶች ያላቸውን የጽሁፍ ችሎታ በንፅፅር ማጥናት ነው፡፡በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በቃላት አጠቃቀምና ምርጫ፣በሰዋስው አጠቃቀም፣በአንቀፅ አደረጃጀት፣በፊደላት ቅርፅ አጣጣልና አጠቃቀም በአማርኛ ቋንቋ አፍፈቶች ከኢ-አፍፈት ተማሪዎች የተሸሉ ሆነው መገኘታቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ በአማርኛ ኢ-አፈፈት ተማሪዎች የተሸሉ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጠዋል፡፡በዚህ ጥናት የምናስተውለው አፈፈትና ኢ-አፈፈት ተማሪዎች በጽሁፍ ክሂል ላይ የተለያየ ውጤት እንደሚያስመዘግቡ ነው፡፡ጥናቱም የተካሄደው በንፅፅር እይታ

ሲሆን በዚህ ጥናት ቢታይ ብላ አጢኚዋ የወሰደቻቸው ዕጩ መምህረኑ በአማርኛ አፈፈትም ሆነ ኢ-አፈፈት ለደረጃው ይመጥናሉ የሚለው ታክሎ ቢታይ፡፡

ተገኝ (2000) አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ ዕጩ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተት ትንተና መፈተሽ ነው፡፡በጥናቱ የተገኘው ውጤት በቋንቋ አጠቃቀም ሥር የተፈፀሙ ስህተቶች የፊዴል አጻጻፍ፣የቃል አመራረጥና አጠቃቀም በቋንቋ አወቃቀር ሥር የተፈፀሙ ስህተቶች የመስተዋድድ አገባብ፣ የዐረፍተ ነገር ስምምነት፣ የአያያዥ አገባብ ፣በቃላት አወቃቀር ስሆን በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ሥር የተፈፀሙ ስህተቶች ደግሞ አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ትምህርተ ጥቅስ፣ትምህርተ አንክሮና ጥያቄ ምልክት የተከሰቱ ናቸው፡፡ሌላው የፅንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች እና መለየት ያልተቻሉ ስህተቶች በዕጩ መምህራኑ ድርሰት ውስጥ ተገኝተዋል፡፡መንስኤውም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተፅዕኖ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች መሆናቸውን ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

ሙሉጌታ (2003 ዓ.ም) በጥናታቸው ዓብይ ዓላማ አድርገው የተነሱት በአርባ ምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ2ኛ ዓመት ዕጩ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ለይተዋል፡፡በጥናቱም የተገኘው ውጤት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት፣አወቃቀር፣የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ ስህተቶች መኖራቸውን አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ ከፍ ብሎ በቀደምት ጥናቶች ቅኝት የተለያዩ ሦስት የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችን ማየት ተሞክሯል፤እነዚህ ጥናቶችም የሚያሳዩት እጩ መምህራኑ በሚጽፉበት ጊዜ ስህተት እንደሚፈጽሙና በመጻፍ ክሂል ላይ ችግር መኖሩን ነው፡፡ነገር ግን እነዚህ እጩ መምህራን ነገ ለተሰለፉለት አላማ በቂ ናቸው?የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡ያየናቸው ጥናቶች ይህንን ጎን ባለማየታቸው ሊጠና የሚገባ ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተመሳሳይ መሰረት (2003 ዓ.ም) እና የአምላክሥራ (2008 ዓ.ም) ባደረጉት ጥናት በአማርኛ ቋንቋ አፈፈትም ሆነ ኢ-አፈፈት ተማሪዎች በተለያየ የክፍል ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶችና የስህተት ምንጮችን ለይተዋል፡፡

ኃይላይ (2011 ዓ.ም) ባደረጉት ጥናት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ችግር አለባቸው፡፡በድርሰት የመፃፍ ትምህርት ረገድ ሀሳባቸውን በጽሁፍ ከመግለፅና በግልም ሆነ በትብብር የመጻፍ ችሎታቸውን ከማዳበር ይልቅ በመልስ አስመራጭ ምዘናዎች አማካይነት ውጤት ማግኘት ይመርጣሉ በማለት፤ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽችግር እንዳለባቸውና ለጽሁፍ ክሂል ያላቸውን ተነሳሽነት ማነስ በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡

ተመስገን (2001 ዓ.ም) የአስራ አንደኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመጻፍ ተዛምዶ መመርመር ሲሆን የተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ከመምህራኑ በተገኘ መረጃ መሰረት የማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎቹ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መካከል ዝምድና የሌለ መሆኑና መምህሩ የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ባማከለ መልኩ ሳይሆን በራሱ ስሜት ብቻ በተማሪዎች ላይ ጫና ያሳደረ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ከዚህ ከፍ ብለን ያየናቸው ጥናቶች በአጠቃላይ የሚስማሙበት አንድ ነጥብ አለ፡፡ይህውም በአማርኛ ቋንቋ ሀሳብን በጽሁፍ የመግለጽ ሰፊ ክፍተት መኖሩን ሲሆን ቀደምት ጥናቶቹ ይህ ችግር ምን አይነት ችግር እንደሆነ እና የችግሩ ምንጭ ምን እንደሆነ ማየት ተሞክሯል፡፡ለችግሩ እንደ መፍትሄ የተቀመጡ አቅጣጫዎች አሉ እነዚህም የማስተማሪያ ዘዴዎች እና የመምህራኑ የግብረ መምስ አሰጣጥ ችግር መሆናቸውን ያየናቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡የዚህ ጥናት አላማ የሆነው ግን ችግሩን መለየት ብቻ ሳይሆን ያሉበትን ደረጃ በማሳየት ለደረጃው ይመጥናሉ የሚለውን ማየት ነው፡፡

ምዕራፍ ሦስት፤የአጠናን ዘዴ

3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት አብይ አላማ የአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የ3ኛ አመት ተመራቂ እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ መፈተሽ ነው፡፡ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ከምርምር ስልቶች አንዱ የሆነውን ንጥል የምርምር ስልትን ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ምክንያቱም በአንድ ነጠላ ቡድን ያተኮር ያለውን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት አድርጎ በገለጻ የሚቀርብ በመሆኑና ለታለመው ጥናት አስፈላጊነቱን በማመን ነው፡፡

3.2 የጥናቱ ዘዴ

ለዚህ ጥናት ተመራጭ የምርምር ዘዴ የሆነው በዋናነት አይነታዊ ሲሆን በደጋፊነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምክንያቱም በፈተና የተገኘው ውጤት የሚተነተነው ሙሉ በሙሉ ቁጥርን መሰረት በማድረግ አይደለም ስለዚህ በፈተና የተገኘው ውጤት በድግግሞሽ እና በመቶኛ ተሰልቶ በገለጻ ቀርቧል፡፡

3.2.1 የተማሪና የተምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት የሚካተቱ ተጠኚዎች በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሥት ከሚገኙ 5 የመንግሥት መምህራን ትምህርት ኮሌጆች መካከል አንዱ የሆነው የአርባ ምንጭ መምህራን ትምህርት ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተመርጧል፡፡ የተመረጠውም አመቺ ንሞና ዘዴን በመጠቀም ነው፡፡ምክንያቱም ይህ ኮሌጅ የሚገኘው አጥኝዋ በምትሰራበት አካባቢ በመሆኑ የምትሰራውን ስራ ሳታስተጓጉል ጎን ለጎን መስራት ያስችላታል፤ በተጨማሪም ጊዜን፣ጉልበትና ገንዘብን ይቆጥባል፡፡ተጠኝዎችን በተመለከተ የ2012 ዓ.ም አማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ላይ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የክላስተር ተመራቂ ዕጩ መምህራን ናቸው፡፡ተመራቂ እጩ መምህራኑ የተመረጡበት ምክንያት ኮርሱን አጠናቀው ወደ ስራ ሊገቡ የተዘጋጁ በመሆናቸው፤የእጩ መምህራኑ ለሦስት ተከታታይ አመታት ተምረው ሲመረቁ ለደረጃው ብቁ መሆናቸውን መፈተሽ ስለሚያስችል ነው፡፡ይህን አላማ ለማሳካት ጠቅላይ ንሞና ዘዴ በመጠቀም በክፍል ውስጥ የሚገኙ ሁሉም አባል ተጠኚ ሆነው ተመርጠዋል፡፡ምክንያቱም በቁጥር 45 ብቻ

በመሆናቸው መረጃ ለመሰብሰብ ሆነ ለመተንተን ብዙም አስቸጋሪ ስለማይሆን እና የጥናቱን ተዓማኒነት ይበልጥ ከፍ ያደርገዋል በሚል ነው፡፡

3.2.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የዚህ ጥናት ዋናና ዝርዝር አላማዎችን መሰረት በማድረግ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የተመረጠውና ተግባር ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ነው፡፡መረጃ መሰብሰቢያ የሆነው በተማሪዎች የተጻፈ ድርሰት/ጽሁፍ ውስጥ ያለውን የይዘት ሥፋትና ጥልቀት፣የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት፣የቃላት አመርረጥና አጠቃቀም፣ የቋንቋውን ህግ (ሰዋስዋዊ) ትክክለኛነት እና የአጻጻፍ ስርአታቸውን በማየት፤እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ደረጃ ለመፈተሽ ያግዛል በሚል ነው፡፡

3.2.2.1 የፈተናው አዘገጃጀት እና እርማት

እጩ መምህራኑ የጽሁፍ ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ አስር (10) የድረሰት መጻፊያ ርዕሶች/ምክንያቶች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፡፡አዘገጃጀቱም የእጩ መምህራኑ ዳራዊ እውቀት፣የሚኖሩበት የማህበረሰቡን የአኗኗር ሁኔታ፣ሀይማኖትንና ጾታን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ የተዘጋጁትም የመጻፊያ ርዕሶች ተገቢነታቸውንና አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥ አንድ ዲግሪና ሁለት ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ባላቸው ሦስት የኮሌጁ መምህራን እና አማካሪ መምህር ተገምግመው አስተያየትና ማሻሻያ ከተሰጠባቸው በኋላ በአቻ ኮሌጆች በተመሳሳይ እጩ መምህርን ላይ ሙከራ ማድረግ ተገቢ ነበር፤ነገር ግን ከወቅቱ ሁኔታ የተነሳ /ኮቪድ 19/ ወረርሽኝ በመከሰቱ ማድረግ አልተቻለም፡፡በተሰጠው አስተያየትና ማሻሻያ መሰረት ተገቢነቱና አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ በመቀጠልም ለተጠኚ እጩ መምህራኑ በክፍል ውስጥ ከሁለት አንቀጽ ባልበለጠ ገላጭ/ተራኪ ድርሰት እንዲጽፉ ተደረጓል፡፡10 የመጻፊያ ርዕሶች/ምክንያቶች ቀርበዋል፡፡10 የመጻፊያ ርዕሶች/ምክንያቶች የቀረቡበት ምክንያት እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በሚገባና በስፋት መግለጽ የሚያስችላቸው ሰፊ አማራጭ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

የፈተናው አስተራረም የሆነው፤ሁላቀፍ የድርሰት እርማት (holistic approach) ሲሆን ከይዘት፣ከሀሳብ አደረጃጀት፣ከቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ከሰዋስውና ትክክለኛነት፣

ከስርአተ- አጻጻፍ አንጻር የተከናወነ ነው፡፡የእርማት አስተማማኝነታቸውን ለመጠበቅና የእርማቱን ፍትሃዊነት በተቻለ መጠን ስሜታዊነት እንዳይንጸባረቅበት ለማድረግ አንድ ዲግሪና ሁለት የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው የኮሌጁ መምህራንን በመጠቀም፤ኃይላይ(2011) ከፋሪስ(2003) እና ከማረው(2005) አሻሽለው የወሰዱት የማረሚያ መስፈርት ተግባር ላይ በማዋል፤የመጻፍ ንዑሳን ችሎታዎች መሰረት በማድረግ በተዘጋጀው በማረሚያ መስፈርትና ውጤት አሰጣጥን በተመለከተ ለመምህራኑ ገለጻ ከተደረገ በኋላ፤የተማሪውን የፈተና ወረቀት ወይም በእጩ መምህራኑ የተጻፉ ድርሰቶች እና የማረሚያ መስፈርቶች ሦስት ሦስት ኮፒ በማድረግ አያይዞ፤ለመምህራኑ በመስጠት በተዘጋጁ ማረሚያ መስፈርቶች መሰረት እንዲያርሙና ውጤት እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ የማረሚያ መስፈርቶችም የጽሁፉ ይዘት ስፋትና ጥልቀት፣የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ሰዋስው ትክክለኛነት እና ስርአተአጻጻፍ አኳያ የተዘጋጀ ነው፡፡በሦስቱ አራሚዎች መካከል የእርማት ተጣጣሚነት መኖሩን ለማየት የCronbach Alpha ቀመርን በመጠቀም ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.929 ሆኗል፡፡ይህም በሦስቱ አራሚዎች መካከል ተጣጣሚነት መኖሩን ያሳያል፡፡

3.2.2.2 የድርሰት ሰነዶች

በድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ከእጩ መምህራኑ የተሰበሰቡ የድርሰት ሰነዶች በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡በፈተናው ወቅት ከቀረቡላቸው አስር የመጻፊያ ርዕሶች/መከንያቶች/ መካከል ሀሳባቸውን በሚገባ መግለጽ የሚያስችላቸውን አንድ ርዕስ በመምረጥ እንዲጽፉ ተደርጓል፡፡በዚህም የተገኙ መረጃዎች የይዘቱ በስፋትና በጥልቀት መግለጽ አለመቻሉ፣የሀሳብ ፍሰት አጠባበቅ፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣የሰዋስው ትክክለኛነትና የአጻጻፍ ስርአታቸው ላይ ያሉ ችግሮችን ማሳየት ችለዋል፡፡



ስዕል. 2 የጥነቱ ጽንሰ ሀሳባዊ ሂደት

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኘው ውጤት በድግግሞሽ እና በመቶኛ ተሰልቶ በገለጻ ቀርቧል፡፡በተጨማሪ የእጩ መምህራኑ ውጤት፤ኮሌጁ ካስቀመጠው ማለፊያ ነጥብ ጋር በማነጻጸር የጉልህነት ደረጃውን ለማሳየት በፓራሜትርካዊ መፈተሻ ጥገኛ ተለዋዋጭ (Dependent) ነጠላ ናሙና (One sample T-test) ተግባር ላይ ውሏል፡፡ይህ ማለት ተመራማሪው ከአንድ ቡድን አንድ ጊዜ መረጃውን ከሰበሰበ በኋላ ያገኘውን መረጃ ቀድሞ ካለ ከሚታወቅ ውጤት ጋር ለማወዳደር ሲፈልግ የሚጠቀመው በመሆኑና ለዚህ ጥናት ተገቢነቱን በማመን ነው፡

በዚህ ጥናት አጥኝዋ ከናሙና የተገኘውን አማካይ ውጤት ቀድሞ ከሚታወቀው ወይም በኮሌጁ ከተቀመጠው የተማሪ ማለፊያ ነጥብ ከመቶ ከ50 በላይ እና ከ50 በታች በመውሰድና በነጠላ ናሙና (one sample t-test) በመጠቀም በምዕራፍ አራት በዲጋፊነት ተንትናዋለች፡፡

3.4 ደረጃ አሰጣጥ

በዚህ ጥናት የእጩ መምህራኑን ውጤት ደረጃ (score) ለመወሰን በጥቅም ላይ የዋለው በአርባምንጭ መምህራን መሰልጠኛ ኮሌጅ የሚጠቀሙትን መነሻ ነጥብ 50% ከመቶ ያመጣ ያልፋል ወይም ማለፊያ ነጥብ አግኝቷል በማለት ነው፡፡ ይህንን መነሻ በማድረግ ከመቶ የመጣውን ውጤት በማየት እንዴት ደረጃ ይሰጥ የሚለው ይወሰናል፡፡

አጥኝዋ ይህንን መነሻ በማድረግ ደረጃ ለመስጠት ከእጩ መምህራኑ በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና በተገኘው ውጤት መሰረት ደረጃ መስጠት ሞክራለች፡፡ደረጃ (score) አሰጣጡ መሰረት የሚያደርገው ጥሩ ጽሁፍ ሊያካትት ከሚገባው መስፈርት አንጻር ማለትም ይዘት፤የሀሳብ አደረጃጀት፤የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፤የቋንቋውን ህግ /ሰዋስዋዊ/ አጠቃቀምና ስርአተ አጻጻፍ መነሻነት በአራት ደረጃ ተከፋፍሎ ተቀምጧል፡፡ፈተናው የታረመው ከሃያ አምስት ሲሆን ወደ መቶ ተቀይሮ 100-80 ከፍተኛ(good) 50-79 መካከለኛ(fair) 49-20 ዝቅተኛ(limited) 19 እና በታች በጣም ዝቅተኛ(weak) በማለት ደረጃ ወጥቶለታል፡፡

ሰንጠረዥ 1፡ የጽሁፍ ችሎታ ደረጃ መወሰኛ

ውጤት	
ከ100	**ደረጃ**
100 — 80	ከፍተኛ
79 — 50	መካከለኛ / በቂ /
49 — 20	ዝቅተኛ
19 — 0	በጣም ዝቅተኛ

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ 1 የጽሁፍ ችሎታ ደረጃ አሰጣጥን በተመለከተ የኮሌጁን ነጥብ አሰጣጥ መነሻ በማድረግ የእጩ መምህራኑ በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ያመጡት ውጤት መሰረት ደረጃ አሰጣጡ የሚሆነው ከ80% በላይ ከፍተኛ ከ50%-79% መካከለኛ/በቂ/ ከ20%-49% በላይ ዝቅተኛ 20% በታች በጣም ዝቅተኛ በማድረግ ደረጃ ተሰጥቷል፡፡

ምዕራፍ አራት፤የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በ2012 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋ እጩ መምህራን ሀሳባቸውን በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታቸውን መፈተሽ ነበር። በሌላ አገላለጽ እጩ መምህራን የጽሁፍ ችሎታ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ ነው፤ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሀሳባችውን በጽሁፍ መግለጽ የሚችሉበት የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተዘጋጅቶ መረጃ መሰብሰብ ተችሏል።ለጥናቱ የተመረጡት 45 እጩ መምህራን ሲሆኑ ፈተና የተቀመጡና ምለሽ የሰጡ 41 እጩ መምህራን ናቸው።ቀሪ 3 ሴቶችና 1 ወንድ በፈተናው ጊዜ ባለመገኘታቸው ከጥናቱ ውጪ ሆነዋል።ስለዚህ ለትንተናው የቀረቡ 41 እጩ መምህራን ውጤት ነው።ይህም ውጤት በእያንዳንዱ ንዑሳን ክሂሎት ያመጧቸው ውጤት ኮሌጁ ካስቀመጠው የማለፊያ ነጥብ ከ50% በላይ ያመጣ ያልፋል፤በታች ያመጣ ይወድቃል የሚለውን የውጤት አሰጣጥ መሰረት በማድረግ በድግግሞሽና በመቶኛ ተተንትኖ እንደሚከተለው ቀርቧል።

4.1.1 የይዘት ስፋትና ጥልቀት መፈተሸ

የጥናቱ የመጀመሪያ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የይዘት ስፋትና ጥልቀት በመቃኘት ግልጽና በተመጣጠነ ዐረፍተ ነገር መልዕክት ማስተላለፍ ይችላሉ?» የሚል ሲሆን ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በጽሁፍ መለኪያ ፈተና የተሰበሰበው መረጃ በንዑስ ክሂል ይዘት ያላቸውን ችሎታ በድግግሞሽና በመቶኛ ተሰልቶ ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዠ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 2 ፡ እጩ መምህራን በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የይዘት ስፋትና ጥልቀት በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ

በፈተና የተገኘ ውጤት	ድግግሞሽ	በመቶኛ	ደረጃ
80-100	2	4.9	ከፍተኛ
50-79	24	58.5	መካከለኛ
20-49	15	36.6	ዝቅተኛ
0-19	-	-	በጣም ዝቅተኛ

በሰንጠረዥ 2 እንደተመለከተው እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የመጻፍ ንዑስ ክሂል በድግግሞሽና በመቶኛ እናገኛለን፡፡ይኸውም በችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኘው ውጤት ከ41 ተጠኚዎች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የተቀመጡ በድግግሞሽ 2 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ የሚያሳየው 4.9%፣ በጥሩ ደረጃ የሚገኙት በድግግሞሽ 24 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 58.5% ያሳያል፡፡በዝቅተኛ ደረጃ የተፈረጁት በድግግሞሽ 15 እጩ መምህራን ሲሆን በመቶኛ 36.6% ሆኗል፡፡ይህም የሚያሳየው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን ከ50% በላይ ያስመዘገቡ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪ በአጋዥነት በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ተሰልቶ የቲ-ዋጋ 1.452 እና P=0.154 ሆኗል፡፡ይህም የሚያሳየው የመጣው ውጤት ከተቀመጠው ማለፊያ ነጥብ ሲነጻጸር ብዙም ልዩነት የለውም ይህም በአባሪ ‹‹ሀ›› ለይ ተመልክቷል፡፡እጩ መምህራኑ የጻፏቸው ድርሰቶች ምን ያህል ደጋፊ እንደሆኑ ለማመሳከሪያነት ቀርቧል፡፡



በመለያ ቁጥር 20 ላይ የተመለከተው ናሙና ድርሰት ከትዕዛዝ ጀምሮ ያለውን ክፍተት ያሳያል፡፡ ትዕዛዙ የሚለው ተራኪ ወይም ገላጭ ድርሰት መጻፊያ ዘዴን ተጠቅመው ድርሰት እዲጽፉ ቢሆንም ትዛዝ ያለማክበር ታይቷል፡፡

የቀረበው ርዕስ "ትመህርት ቤቴ"የሚል የመጻፊያ ርዕስ ሲሆን፤ይህን ርዕስ ለመግለጽ የቀረቡት ሀሳቦች ተገቢነት ያላቸው አይደሉም፡፡ ማስተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- …..ወግ ማረግ ያየሁበት፣

ኩራቴ ነው ለእኔ ትምህረት ቤቴ፡፡

ከእናት ከአባት በላይ ያስረዳኝ……እያለ ይቀጥላል፡፡

4.1.2 የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት መመርመር

የጥናቱ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት አለውን?» የሚል ሲሆን ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መረጃ መሰብሰቢያነት በቀረበው የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና አማካኝነት የተሰበሰበው ውጤት የሚያሳየው፤ በዚህ ንኡስ ክሂል ላይ እጩ መምህራኑ ያለቸው ችሎታ ፈተናውን መሰረት በማድረግ በመቶኛ እና በድግግሞሽ ተሰልቶ ደረጃው ኮሌጁ ባስቀመጠው ከ50% በላይ ያመጣ የማለፊያ ነጥብ ያለውና ከ50% በታች ያመጣ ደግሞ ያላለፈ በሚል ደረጃ ይሰጣቸዋል፡፡በዚህም ጥናት ይህንን መነሻ በመድረግ ውጤት ወይም ደረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 3 እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ

በፈተና የተገኘ ውጤት	ድግግሞሽ	በመቶኛ	ደረጃ
80-100	2	4.9	ከፍተኛ
50-79	17	41.5	መካከለኛ
20-49	21	51.2	ዝቅተኛ
0-19	1	2.4	በጣም ዝቅተኛ
ድምር	41	100%	

በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የሀሳብ ፍሰት ተያያዥነት አለውን? የሚል ሲሆን ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ በፈተና የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ከ41 እጩ መምህራን ውስጥ በድግግሞሽ 2 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 4.9% መሆኑን ያሳያል፡፡በጥሩ ደረጃ ከላይ የሚገኙ በድግግሞሽ 17 ሲሆኑ በመቶኛ 41.5% ነው፡፡በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙት ደግሞ 21 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ የሚያሳየው 51.2% መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ይህም የሚሳየው በዚህ ንዑስ ክሂል ከግማሽ በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን ከ50% በታች ውጤት በማስመዝገብ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ማየት ተችሏል፡፡በአጋዥነት ነጠላ ናሙና ጥናት (one sample t-test) ተሰልቶ፤የቲ-ዋጋ (-0.726)እና (P =0.456) ሆኗል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ስታቲስቲካዊ ጉልህ ልዩነት መኖሩን ነው፡፡የተገኘው ነጥብ በትምህርት ሚኒስተር ከተቀመጠው ማለፊያ ነጥብ ጋር ሲነጻፀር ከ50% በታች የሆነ ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ስለዚህ የማለፊያ ውጤት አላገኙም የሚል ድምዳሜ ያሳያል ይህም በአባሪ‹‹ለ››ተመልክቷል ፡፡ ከመጠናዊ መረጃ ትንተና ባሻገር የተማሪዎችን ናሙና ድርሰት በመጠቀም በእማኝነት ቀርቧል፡፡

እጩ መምህራኑ የጻፏቸው ድርሰቶች ምን ያህል ደጋፊ እንደሆኑ በእማኝነት ቀርቧል፡፡



ከዚህ ከፍ ብሎ በመለያ ቁጥር 9 የቀረበው በእጩ መምህራን የተጻፈ ናሙና ድርሰት ነው፡፡ ከሀሳብ አደረጃጀት አንጻር ሲታይ በመጀመሪያው አንቀጽ ስለጀግንነት ማውራት ሞክሯል፡፡ በሁለተኛው አንቀጽ ደግሞ ኢትዮጵያ በቀኝ ያልተገዛች ሀገር መሆኗን ጀመር አድርጎ፤ቀጥሎ በዚያው ኢትዮጲያ ለሱ ያላትን ፍቅር ገልጾ ሳያበቃ በዘር፣በብሄር፣በሃይማኖት የሚል ነገር አመጣ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠኝ አጩ መምህር ከቀረበለት አስር አማራጭ ምክንያቶች መካከል ለሱ በሚመች መልኩ በመረጠው ርዕስ እንዲጽፍ ነው የተደረገው፡፡በዚህም መሰረት ዕጩ መምህሩ የመረጠው ርዕስ ‹‹የእናት ፈቅር››የሚል ሲሆን የተጻፈው ድርሰት ግልጽነት የጎደለው፣ተጠየቃዊ የሆነ አደረጃጀት የማይታይበት

ያነሳውን ርዕሰ ጉዳይ ወደጎን በማለት የጻፈው ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር የማይገናኝ መሆኑን በናሙናነት የቀረበውን ጽሁፍ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡

4.1.3 የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መፈተሽ

የጥናቱ ሦስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ ‹‹ እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል? ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በተሰጣቸው የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና መሰረት የተሰበሰበው መረጃ በድግግሞሽና በመቶኛ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡የደረጃ አሰጣጡም መነሻ የሚያደርገው በኮሌጁ ውጤት አሰጣጥ መሰረት ነው፡፡

ሰንጠረዥ 4 እጩ መምህሩኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቃላት አመራራጥና አጠቃቀማቸው በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ

በፈተና የተገኘ ውጤት	ድግግ ሞሽ	በመቶኛ	ደረጃ
80-100	1	2.4	ከፍተኛ
50-79	16	39.0	መካከለኛ
20-49	24	58.5	ዝቅተኛ
0-19	-	-	በጣም ዝቅተኛ
	41	100%	

በሰንጠረዥ 4 እንደተገለጸው እጩ መምህራኑ የሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀማቸው ምን እደሚመስል ከጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና በተወሰደው ውጤት መሰረት በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ከ41 እጩ መምህራን መካከል በድግግሞሽ 1 እጩ መምህር ሲሆን በመቶኛ 2.4% ነው፡፡በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ በድግግሞሽ 11 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 39% ነው፡፡በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ወይም ከ50% በታች ያስመዘገቡ በድግግሞሽ 24 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 58.5% ሲሆን፤ከ50 በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መገንዘብ ተችሏል፡፡በአጋዥነት በነጠላ ናሙና (One sample t-test)

ተሰለቶ፤የተገኘው የቲ-ዋጋ (-1.925) እና የጉልህነት ደረጃ (p = 0.061) ሆኗል፡፡ይህም ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል በአባሪ ‹‹ሐ›› ተመልክቷል፡፡



በመለያ ቁጥር 37 በቀረበው በእጩ መምህራን የተጻፈ ናሙና ድርሰት ውስጥ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም አንጻር ማየት ተሞክሯል፡፡በርካታ የቃላት ድግግሞሽ ይታያሉ፡፡ከቃላት አመራረጥ አንጻር በጥንቃቄ የተመረጡ አይደሉም፡፡ለአንባቢ ስሜት የሚፈጥሩ አለመሆናቸውን ከናሙና ድርሰቱ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ፡- “እናቴ” እና “እኔ” እነኝህ ቃላት ተደጋግመው ተጽፈው እናገኛቸዋለን፡፡

ሀ/ <u>እናቴ እኔን ከወለደች</u> ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያላት ፍቅር በጣም ልዩ ነው፡፡

“እኔን” የሚለው ቃል አላስፈላጊ ነው፡፡ከወለደችኝ ቢባል በቂ ነው፡፡

…ያላት ፍቅር <u>በጣም</u> ልዩ ነው፡፡ለእኔ ያላት ፍቅር ልዩ ነው፡፡ቢባል ትንሽ የተሸለ ይሆናል፡፡በአጠቃላይ አላስፈላጊ የቃላት ክምችት ይታይበታል፡፡

ለ/ እናቴ እኔን ያለ አባት ያለ ወንድም ያለ ማንም ብቻዋን አሳደገችኝ፡፡

ሐ/ ለማንም እራሷን የምተሰዋ የተቸገሩትን የምትረዳ ለክፎዎች የማትቀና ብቻዋን ያለማንም እርዳታ ለዚህ ደረጃ ያበቃችኝ ብቸኛ ፍቅር ነች፡፡

አረፍተ ነገሩ ከቃላት አመራረጥ ችግር የተነሳ ምን ለማለት እንደተፈለገ መረዳት አዳጋች ነው፡፡

4.1.4 የቋንቋውን ህግ (ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት) መፈተሽ

የጥናቱ አራተኛ መሰረታዊ ጥያቄ እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቋንቋ ህግ ወይም ሰዋስዋዊ ትክክለኛነትን ይጠብቃሉ? የሚል ሲሆን በመረጃ መሰብሰቢያነት በተመረጠው የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና መሰረት የተሰበሰበውን ውጤት መነሻ በማድረግ በድግግሞሽና በመቶኛ ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ ተመልክተዋል፡፡

ሰንጠረዥ 5 እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የቋንቋውን ህግ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት በተመለከተ ደረጃ ማሳያ

በፈተና የተገኘ ውጤት	ድግግሞሽ	በመቶኛ	ደረጃ
80-100	1	2.4	ከፍተኛ
50-79	15	36.6	መካከለኛ
20-49	23	56.1	ዝቅተኛ
0-19	2	4.9	በጣም ዝቅተኛ
	41	100%	

ከሠንጠረዥ 5 እንደሚያመለክተው በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ በተገኘው ውጤት መሰረት እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድረሰት ውስጥ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት በከፍተኛ ደረጃ ይጠብቃሉ በሚል የተገኘ ውጤት በድግግሞሽ ከ41 እጩ መምህራን መካከል 1 ሲሆን በመቶኛ 2.4%፣በጥሩ ደረጃ የሚገኙ በድግግሞሽ 15 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 36.6% ሆኗል፡፡በዝቅተኛ ደረጃ የተመዘገቡ በድግግሞሽ 23 እጩ መምህራን ሲሆኑ

በመቶኛ 56.1% ነው፡፡ይህ የሚያሳየው ከ50% በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ውስጥ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል፡፡በአጋዥነት በነጠላ ናሙና (One sample t-test) ተሰለቶ፤የተገኘው የቲ-ዋጋ (-1.854) እና p=0.070 ሆኗል ይህም በአባሪ ‹‹መ›› ተመልክቷል፡፡ይህም የሚያሳየው ጉልህ ልዩነት መኖሩ ነው፡፡ እጩ መምህራኑ ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ናሙና በመውሰድ ለእማኝነት ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ከዚህ በላይ በመለያ ቁጥር 13 በቀረበው ናሙና ድርሰት ከሰዋስው አንጻር ሲታይ ፡-

ለምሳሌ፡- ሀ/ <u>በልጅነት</u> እኔ የማልመውና …..

ቢሆን የተሸለ የሚሆነው (በልጅነቴ)
"በልጅነቴ" የሚለው ቃል በውስጡ (እኔ) የሚለውን የባለበት አመልካች የያዘ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ አያስፈልገውም፡፡
ከአረፍተ ነገር አወቃቀር አንጻር ግድፈት አለው ማለት ነው፡፡

ለ/ <u>እኔ ተምሬ</u> ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ…

ሊሆን የሚገባው ትምህርቴን ከጨረስኩ በኋላ …

አላስፈላጊ የቃላት ድረታዎች ይታያሉ፡፡

ሐ/ ችግሮች መሐል ተጋፍጨ ለዝ <u>አበቃሁኝ</u> ፡፡

ችግሮችን ተጋፍጬ ለዚህ በቃሁኝ፡፡

4.1.5 የ አጻጻፍ ሥርዓታቸውን መፈተሽ

የጥናቱ አምስተኛ መሰረታዊ ጥያቄ እጩ መምህራኑ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ሥርዓተ አጻጻፋቸው ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ይህንን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ በተሰጣቸው የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና አማካኝነት የተሰበሰበው ዉጤት በሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 6 እጩ መምህራኑ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ስርአተ አጻጻፋቸውን በተመለከተ የተሰጠ ደረጃ

በፈተና የተገኘ ውጤት	ድግግሞሽ	በመቶኛ	ደረጃ
80-100	1	2.4	ከፍተኛ
50-79	7	17.1	መካከለኛ
20-49	27	65.9	ዝቅተኛ
0-19	6	14.6	በጣም ዝቅተኛ
	41	100%	

ሠንጠረዥ 6 እንደሚያሳየው እጩ መምህራኑ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የስርዓተ አጻጻፋቸው ምን እንደሚመስል በጸሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና በተሰበሰበው ውጤት መሰረት በከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ እጩ መምህራን በድግግሞሽ 1 ሲሆን በመቶኛ 2.4% መሆኑን ያሳያል፣በጥሩ ደረጃ ላይ የሚገኙ በድግግሞሽ 7 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 17.1% ሆኗል፤በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ 27 እጩ መምህራን ሲሆኑ በመቶኛ 65.9% መሆኑን ያሳያል፡፡ይህ የሚያመላክተው ከግማሽ በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን ከ50% በታች ውጤት ማስመዝገባቸውን መረዳት ተችሏል፡፡ በአጋዥነት ነጠላ ናሙና(One sample t-test) ተሰለቶ የተገኘው የቲ-ዋጋ (-5.0317) እና p=000 ሆኗል፡፡ይህም የሚያሳየው ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ነው፡፡በአባሪ‹‹ሠ»ላይ ተመልክቷል፡፡በዕጩ መምህራኑ የተጻፉ የናሙና ድርሰቶች በእማኝነት ቀርቧል፡፡



መለያ ቁጥር 16 የተወሰደው ናሙና ድርሰት ከጽህፈት ንዑስ ክሂል አንዱ የሆነው ከሥርዓተ አጻጻፍ አንጻር ታርሞ በአይነታዊ ትንተና ተደርጓል፡፡

የመጻፊያ ወረቀት አጠቃቀም ተገቢነት የለውም፡፡የተጻፈው ዳር እስከ ዳር መሆኑን ከናሙና ድርሰቱ ማየት ይቻላል፡፡

አዲስ ሀሳብ ሲጀምር አንቀጽ መለያ የለውም፡፡

የእጅ ጽሁፍ አጣጣልና የሳድስና ሳልስ አጠቃቀም ላይ ሰፊ ግድፈት ይታያል፡፡

ለምሳሌ፡ -እድሜ (እድሜው) ስደርስ (ሲደርስ) ለላም (ሌላም) ልገባው (ሊገባው) ልገነዘብ (ሊገነዘብ)

-ትምህርት ቤት <u>ከመግባት</u> (ከመግባቱ) በፊት ምንም ላያውቅ ወይም ላይረዳ ይችላል፡፡

ከፊደል አጣጣልና ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አንፃር አራት ነጥብ የሚባል የለም፡፡ሁለት ነጥብም በተገቢው ቦታ እየተጠቀመ አይደለም፡፡

ለምሳሌ፡-ትምህርት ቤት የሰው ልጅ የሚቀረፅበትና የሚቀየርበት <u>ነው፡</u>

ምሳሌው እንደሚያመለክተው ሁለት ነጥብ የተጠቀመው አራት ነጥብ ሊጠቀምበት በሚገባው ቦታ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ “እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ መፈተሽ፡፡” የሚል ሲሆን ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ ለእጩ መምህራኑ ድርሰት የመጻፍ ቸሎታ መለኪያ ፈተና ተሰጥቶ አምስቱን ንዑሳን ክሂሎች ይዘት፣የሃሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣የቋንቋ ህግ/ሰዋስው/እና ስርአተ አጻጻፍ በመጠቀም በተዘጋጀ ዝርዝር ማረሚያ መስፈርት ታርሞ የተገኘው ውጤት የኮሌጁን ውጤት አሰጣጥ መሰረት በማድረግ በመቶኛና በድግግሞሽ ተሰልቶ ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 7 የእጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ደረጃ ማሳያ

ደረጃ	ድግግሞሽ	በመቶኛ
ከፍተኛ	1	2.4
መካከለኛ	15	36.6
ዝቅተኛ	25	61
በጣም ዝቅተኛ	-	-
ድምር	41	100

ሠንጠረዥ 7 እንደሚያሳየው እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኘው ውጤት በኮሌጁ ውጤት አሰጣጥ መሰረት በመቶኛ 2.4 ያስመዘገቡ ከፍተኛ ሲሆን በድግግሞሽ 1 እጩ መምህር ብቻ መሆኑን ፤በመቶኛ 36.6 ያስመዘገቡ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የተመዘገቡ ሲሆን በድግግሞሽ 15 እጩ መምህራን መሆናቸው፤በመቶኛ 61.0% ያስመዘገቡ ዝቅተኛ ሲሆን በድግግሞሽ 25 እጩ መምህራን መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

ይህ የሚያሳየው የእጩ መመህራኑ የመጻፍ ችሎታ ያለበት ደረጃ ፈተናውን ከተፈተኑ እጩ መመህራን መካከል ከመቶ 61% የሚሆኑ ዝቅተኛ ወይም ከ50 በታች ያስመዘገቡ ናቸው፡፡በሌላ አገላለጽ ከ41 እጩ መምህራን 25 ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከ50 በታች

ያስመዘገቡና ከኮሌጁ ውጤት አሰጣጥ ጋር ሲነጻጸር ማለፍ የማይችሉ መሆናቸውን ነው የሚያመላክተን፡፡ ድምዳሜው

የሚሆነው እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ የላቸውም የሚል ይሆናል፡፡ስእል 4 ይመልከቱ፡፡



ስዕል. 3 የእጩ መምህራኑ ደረጃ ማሳያ

በአጋዥነት ከዚህ በታች እጩ መምህራኑ በፈተናው ያገኙትን ውጤት ኮሌጁ ካስቀመጠው ማለፊያ ነጥብ ጋር በማነጻጸር በነጠላ ናሙና (One sample t-test) ተሰልቶ የጉልህነት ደረጃ ማየት ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ 8፡ እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ትንተና ማሳያ።

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ -ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	11.4632	3.209	-2.069	40	0.045

ሰንጠረዥ 8 እደሚያመለክተው እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ለመፈተሽ በተሰጠው ፈተና እያንዳንዱ ንዑስ ክሂል የታረመው ከ5 ሲሆን የአምስቱ ንዑሳን ክሂሎች ውጤት (25) ይሆናል።ይህ ጥቅል ውጤት በኮሌጁ ከተቀመጠው ማለፊያ ነጥብ 50% ጋር ለማነጻጸር፤የ(25) 50% የሚሆነው (12.5) ነው።በዚህ መሰረት በእጩ መምህራኑ በተጻፉ ናሙና ድርሰቶች ከተሰበሰበው ውጤት ጋር ሲነጻጸር የተገኘው አማካይ ውጤት(m=11.4632) እና መደበኛ ልይይት (sd=3.209) ይህ ውጤት የእጩ መምህራኑ የማለፊያ አማካይ ውጤት (12.5) ወይም ከመቶ 50 ሲነጻጸር በባለሁለት ጫፍ (2-tailed) ነጠላ ናሙና (One sample t-test) ተሰለቶ፤የተገኘው የቲ-ዋጋ (-2.069) እና የጉልህነት ደረጃ p=0.045 ሆኗል፡ይህ የሚያሳየው እጩ መምህራኑ በፈተና ያስመዘገቡት ውጤት ኮሌጁ ካስቀመጠው ማለፊያ ነጥብ ጋር ሲነጻጸር ጉልህ ለዩነት መኖሩን ማየት ተችሏል።

4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተመራቂ እጩ መምህራን ሀሳባቸውን በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ መፈተሽ ነበር። ከዋናው አላማ መነሻ በማድረግ አምስት መሰረታዊ ጥያቄዎች

ተነድፈዋል፡፡እነዚህም እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ የይዘት ስፋትና ጥልቀት ምን ይመስላል? የሀሳብ ፍሰትና ተያያዥነት አለውን? የቃላት አመራረጥና አጠቃቀማቸው ምን ይመስላል? የቋንቋ ሰዋስው ትክክለኛነት ይጠብቃሉ? ስርዓተ አጻጻፋቸው ምን ይመስላል? የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ዋናና ዝርዝር አላማ ለማሳካት የተመረጡ ተጠኝዎች 45 ሲሆኑ በክፍል ውስጥ ተገኝተው ፈተናውን የተፈተኑ 11 ወንዶች እና 30 ሴቶች በድምሩ 41 እጩ መምህራ ናቸው፡፡ቀሪ ተማሪዎች 1 ወንድና 3 ሴቶች በድምሩ 4 እጩ መምህራን በክፍል ውስጥ ተገኝተው ባለመፈተናቸው ከጥናቱ ውጪ ሆነዋል፡፡ 41 እጩ መምህራን በአንድ ቡድን የተደራጁ ናቸው፡፡የተመረጠውም የጥናቱ ንድፍ ቅኝታዊ ገላጭ ሲሆን፣በጥናቱ ሂደት ለእጩ መምህራኑ አንድ ጊዜ የጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና ተሰጥቶ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተገኘውም መረጃ በድግግሞሽና በመቶኛ ተሰልቶ በአይነታዊ በገለጻ ቀርቧል፡፡ በደጋፊነት መጠናዊ የምርምር ዘዴ ተግባር ላይ የዋለ ሲሆን በፈተና የተሰበሰቡ መረጃ በነጠላ ናሙና (One sample t-test) ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡

የጥናቱ ዋና አላማ እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፉ የመግለጽ ችሎታቸውን መፈተሽ ነበር፡፡ይህን አላማ ለማሳካት ከእጩ መምህራኑ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና የተወሰደ ውጤት መነሻ በማድረግ ያሉበትን ደረጃ የኮሌጁን ውጤት መወሰኛ በመጠቀም ማሳየት ተሞክሯል::ይህም በፈተና የተገኘው ውጤት የታረመው እያንዳንዱ የመጻፍ ንዑስ ክሂል ከ5 ሲሆን በድምሩ 25 ይሆናል፡፡በእያንዳንዱን ክሂል 5 የተገኘው ውጤት በመቶኛና በድግግሞሽ ተሰልቶ ተቀምጧል፡፡በጥቅሉ ከ25 የተገኘውን የንዑሳን ክሂሎች ውጤትም ወደ መቶ ተቀይሮ በድግግሞሽና በመቶኛ ተቀምጧል፡፡በመጨረሻም እጩ መምህራኑ በጽሁፍ ችሎታ መለኪያ ፈተና የተገኘው ውጤት ኮሌጁ ከስቀመጠው ማለፊ ነጥብ ጋር በማነጻጸር ያለውን የጉልህነት ደረጃ ማየት ተችሏል፡፡ከተገኘው ውጤት በመነሳት በእያንዳንዱ ንዑስን ክሂሎች ላይ እንደሚከተለው ማብራርያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በዚህ ጥናት ማረጋገጥ እንደተቻው እጩ መምህራኑ በሚጽፉት ድርሰት ውስጥ በመጻፍ ክሂል ይዘት ከሌሎቹ የተሸለ ውጤት የተመዘገበ ቢሆንም ቀሪ አራቱ የመጻፍ ክሂሎች ላይ ችግሩ እንዳለባቸው ማየት ተችሏል፡፡ከንዑስ ክሂል ይዘት አንጻር ስንመለከት ከ50%

በላይ የሚሆኑ እጩ መምህራን በኮሌጁ ውጤት አሰጣጥ መሰረት ያለፉ ሲሆን የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም እና ከሰዋስው አንፃር ሲታይ ያስመዘገቡት ውጤት ተቀራራቢነት እንዳላቸው ያሳያል፡፤ይህም በቅደም ተከተል ከ41 እጩ መምህራን መካከል 51.2%፣58.5%፣56.1 የሚሆኑ እጩ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ማየት ተችሏል፡፡በሌላ በኩል የመፃፍ ንኡስ ክሂል ሥርዓተ አጻጻፍ ስንመለከት ከሁሉም የመጻፍ ንኡሳን ክሂሎች ውጤቱ ያነሰና ችግሩ የጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህም ከ41 እጩ መምህራን መካከል በድግግሞሽ 27 በመቶኛ ስሰላ 65.9% የሚሆኑ እጩ መምህራን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ በትንተናው ተረጋግጧል፡፡ከዚህ ጥናት የምንረዳው እጩ መምህራኑ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችግር እንዳለባቸው ነው፡

በተመሳሳይ በቀደሚት ጥናቶች ማየት እንደተሞከረው ተማሪዎች በሚጽፉት ጽሁፍ ወይም ድርሰት ውስጥ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም ፣የቋንቋ አወቃቀር የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች መኖራቸው (ሁሴን 2009)፣(ተገኝ (2000)፣ (መሰረት 2003)፣(ክፍሌ 1986)፣(ሙሉጌታ 2003) እና (የአምላክሥራ 2008) እነዚህ ቀደሚት ጥናቶች እንደሚያሳዩት የአማርኛ ቋንቋ አፈፊትን ሆኑ ኢ-አፈፊት በሌላ በኩል ወንዶችም ሆኑ ሴት ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የችግሩ ዓይነትና መጠን ይለያይ እንጂ ችግሩ መኖሩን እና ሊሰራበት እንደሚገባ አሳይተዋል፡፡ለነዚህ ችግሮች እንደመነሻ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የተጠቀሱት፡-

የማስተማሪያ ዘዴ፣የመርጃ መሳሪያ አዘገጃጀት እና የሚዘና አሰጣጥ ሂደት እንደምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡(ተመስገን 2001)፣(ራሄል 2010)፣(የአምላክሥራ 2008)፣(ኃይላይ 2011) እና (ተገኝ 2000)፡፡ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ከማሻሻል ረገድ ትልቅ ሥፍራ ያለው ነው፡፡ለተማሪዎች የሚሰጡ የምላሽ ዐይነቶች፣የሚንጠቀምበት ቦታ እና የሚንጠቀሚበት ጊዜ አንዱ የችግሩ መነሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል (የሺሀረግ (2009)፣(ዳዊት 2008) እና (እታለማው 2006)፡፡

ሌላው እንደምክንያት ሊነሳ የሚችለው የአፍመፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የውስጥ ቋንቋ ተጽዕኖ፣የሥነ ልቦናና የማህበራዊ ሁኔታ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል (ተገኝ 2000)፣(መሰረት 2003)፣ (ሙሉጌታ 2003) በማለት በጥናታቸው አሳይተዋል፡፡

ተማሪዎች በዝቅተኛ ደረጃ አጣርተው ሊመጡ የሚገባቸውን ስህተቶች ወይም ችግሮች ትኩረት ሳይሰጣቸው እስከ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እንዲዘልቁ መሆኑ አንዱ ምክንያት ሊሆን ይችላል በማለት (ተስፋዬ 1988) እና (ባዬ 2009) ይንን ሀሳብ ይደግፉታል፡፡
ከዚህ በላይ ያየናቸው ሁሉም ጥናቶች የተደረጉት በሀገር ውስጥ በተለያ አከባቢና በክፍል ደረጃ ሲሆን የተገኘው ውጤት ከዚህ ጥናት ጋር አንድ ያደርጋቸዋል፡፡ይህ የሚያመላክተን በጥናቶች የተገኙት ችግሮች ሀገር አቀፋዊ ችግር መሆናቸውን ጠቋሚነት አላቸው፡፡ስለዚህ ይህ ችግር የአንድ አከባቢ ወይም የአርባምንጭ ትምህርት ኮሌጅ ብቻ ነው ማለት አይቻልም፡፡ችግሩ አገራዊ ገፅታ ያለው ይመስላል፡፡እናም ሊሰራበት ይገባል፡፡

በዚህ ጥናት የተካተቱ ተጠኚ እጩ መምህራን በ2012 ዓ.ም ተመራቂ ሲሆኑ በጊዜ ማጠናቀቅ ያልተቻለው የኮረና ቫይስ ወረርሽኝ በመከሰቱ ነው፡፡መረጃው በሚሰበሰብበት ሰዓት በደረጃው የተመደበላቸውን ትምህርት አጠናቀው ሊመረቁ ጥቂት ጊዜያት የቀራቸው ሲሆን፤ በቀራቸው የትምህርት ጊዜ የመጻፍ ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ ብሎ ለማመን ያዳግታል፡፡ስለዚህ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ በቋንቋው የጽሁፍ ክሂል ማስተማር ይችላሉ ተብሎ እንደሚታሰበው ሳይሆን የመጻፍ ችሎታቸው እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የጥናቱ ግኝት ይጠቁማል፡፡

ምዕራፍ አምስት፤ ማጠቃለያና አስተያየት

5.1 ማጠቃለያ

ምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለጸው ከአጥኚዋ የማስተማር ልምድ እና ከተለያዩ ከመስኩ ምሁራን ሀሳብ ለመረዳት እንደተቻለው እጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችግር ይታይባቸዋል፤የሚለውን ሀሳብ ይዞ በመነሳት እጩ መምህራኑ ለታችኛው/ለአንደኛ ደረጃ መምህርነት የታጩ ሲሆን፤ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸው ምን ይመስላል?ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?የሚለውን መፈተሽ ተሞክሯል፡፡በናሙናነት ከተመረጡ ተመራቂ ዕጩ መምህራን ውስጥ አብዛኛዎቹ በተሰጠው ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የተገኘው ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ይህ የሚያሳየው በታችኛው የክፍል ደረጃ ሊያውቋቸው የሚገባቸውን መሰረታዊ የሆኑትን የጽሁፍ ክሂል አለባውያን ማለትም ይዘት፣የሀሳብ አደረጃጀት፣የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣የሰዋስው አጠባበቅና ስርአተአጻጻፍ ለይተው አለመምጣታቸውን ያሳያል፡፡ስለሆነም በጥናቱ የተካተቱ እጩ መምህራን የመጻፍ ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡

5.2 አስተያየት

የጥናቱ አቅራቢ የእጩ መምህራኑ የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ በማለት የሚከተሉትን አስተያየቶችን ዘርዝረዋል፡፡

ሀ/ መምህራኑ የእጩ መምህራኑን የመጻፍ ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ከትምህርቱ ይዘት እና ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር በማጣጣም ቢጠቀሙ፡፡

ለ/ መምህራኑ እጩ መምህራኑ በሚጽፏቸው ጽሁፎች ላይ ተገቢውን ምጋቤምላሽ ቢሰጡ እና ደጋግመው እንዲጽፉና እንዲለማመዱ ቢደረግ፤ተነሳሽነታቸው ከፍ ሊል ይችላል፡፡

ሐ/ በየደረጃው የሚማሩ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ክሂል መለኪያ ደረጃ እንድኖር ቢጠና እና ተማሪዎች እየተመዘኑ ለደረጃው ብቁ እየሆኑ ቢያልፉ ውጤታማ መሆን ይችላሉ ብዬ አስባለሁ፡፡

መ/ በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የማጠቃለያ /መግቢያ ፈተና ውጤት ዝቅተኛ ያስመዘገቡ ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ እንድገቡ ይደረጋል፡፡ይህም ጥናት የሚፈልግና አሁን በተገኘው ውጤቱ ላይ ተፅዕኖ ያደርሳል ብዬ አምናለሁ፡፡

ሠ/ ለእጩ መምህራኑ ማሰልጠኛ የሚዘጋጁ ሞጁሎች የሶስቱ አመት ብንመለከት‹‹የጽሁፍ ክሂልን እንዴት ማስተማር ይቻላል›› የሚለው ላይ ያተኮረ ነው፡፡ከዚህ ባለፈ እጩ መምህራኑ ይዘው የመጡትን በማየት ማጠናከሪያ መስጠት የሚያስችል ይዘት ቢኖረው የተሸለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡፡

ዋቢ ጽሁፎች

መሰረት ጣፋ (2003) ። *በሮማያና በአዴሌ ክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈፅሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና* (ያልታተመ)

ሙሉጌታ አብስር (2003) ።*በአርባምንጭ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርትክፍል አፋቸውን በጋሞኛ ቋንቋ የፈቱ የሁለተኛ ዓመት የክላስተር ዕጩ መምህራን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ትንተና* (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)

ማረው ዓለሙ (2007) ። *በሳል ደርሰት ማስተማሪያ*፡አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

በድሉ ዋቅጅራ (2007) ።*በስነ ፅሑፍ ቋንቋን ማስተማር*፡ አዲስ አበባ፣አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርግት።

ባዬ ይማም (2000) ።*የአማርኛ ሰዋስው*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣በአ.ማተሚያ ቤት።

ባዬ ይማም (2009) ።*የአማርኛ ሰዋስው*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣በአ.ማተሚያ ቤት።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981) ።*ስነልሳን እና ቋንቋን ማስተማር*፡ (ያልታተመ)

ያለው እንዳውቅ (2009) ።*የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች አተገባበር*፡ አዲስ አበባ የንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አማረ ማሞ (1986) ።*የልበወለድ ድርሰት አጻጻፍ መሠረታዊ መመሪያ*፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አስካለ ማናዬ (2001) ። *ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች በመምህራንየሚሰጡ ምላሾች የተማሪዎን ድርሰት መጻፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያላቸው ተጽእኖ*

:: (ያልታተመ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)::አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣አዲስ አበባ::

ክፍሌ ሀብተ ማርያም (1986) *:: የሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለፅ ችሎታ መገምገም* :: (ያልታተመ ለሁለታኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት)

ዳዊት ፍሬህይወት (2008):: *የመምህር-ተማሪ ምክክረ እና የመምህር የጽሁፍ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ላይያለው ተጽዕኖ*: (ያልታተመ ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግ ሪማሟያ ጥናት)

ኃይላይ ተስፋይ (2011) :: *የአማራጭ ምዘናዎች የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና ፣በአርባምጭ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋና ስነፅሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍልየአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ተተኳሪነት* (ያልታተመ)

Anderson, V. (2005) *Prediction and Language Learning*. Longman Group.

Bachman, L.F. (1990).*Fundamental consideration in Language Testing*. Oxford. Oxford University press.

Badger, R. (2000) *A Process-genre Approach to Teaching Writing*. London: Springe

Byrne, D. (1988). *Teaching Writing Skills* .London.Longman.Group; UK Limited.

Grab, W.and Kalan, R.(1996).*Theory and Practice of Writing*. London: Addison Wesley Longman

Hedge, T. (1988). *Writing*. Oxford: Oxford University Press.

Kroll, B. (1990).*Second Language Writing* :Research Insightsfor Classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Nunan, D. (1999).*Task Based Language Teaching* .Cambridge University Press.

Nunan, D. (1989). *Designing Communicative Tasks and Activities*. Oxford: Oxford University Press

Ur, P. (1996). *A Course in Language Teaching: Practice and Theory*. Cambridge: Cambridge University Press

Widdowson. (1990).*Teaching Language as Communication*. Oxford. Oxford Universit Press

አባሪዎች

በተማሪዎች የተጻፉ የደርሰት ሰነዶች



(2) የእናቴ ፍቅር   ግጥም ድርሰት

- እናቴ ነሽ መመኪያዬ ናት ለኔ ሁሌ
- እግዚአብሔር ያሳደገኝ በፍቅርና በመልካም
- ዩኒፎርም ስለሆነ ሁሉ በእርግጥ
- እናቴ ናት እግዚአብሔር መስጠት ነው
- በፍቅር ምን እንደሆነ ገና ልጅ ነኝ
- ለመኖር እንደ እንዲህ ሳልፈራ
- እንደ እንዲህ በፍቅር ምን እንደሆነ
- እናቴ እናቴ እናቴ

ሰላም ለአለም ልጆች

፡ሰላም ለአለም ልጆች የሚያስፈልገው ለምን ነው ?
ሀገራችን በሠላም መኖሯ ሰላም የአለም ልጆች ሰላምን እንዲያገኙ መሆኑን እንረዳለን ሰላም ካለ ሁሉም ነገር ሰላም ካለ ጤና ያለው ሰላም ለአለም ልጆች እንደ [illegible] በጣም ወሳኝ ነው፡
ተማሪዎች እንደ እኔ ከዚህ በፊት እንደ ሀገር ጠቃሚ እና ሰላም ለአለም ልጆች በጣም ሰላማዊ ምንጭ የሆነ [illegible]
ከላይ ለአለም ልጆች ሠላ በጣም አስፈላጊ ነው፡
ሁሉም ሠላምን ጤናን ፍቅርን እንመኛለን፡፡

~~ስዕ~~ ድርሰት መጻፍ   ስዕላዊ ድርሰት

ተመ የድርሰት ርዕስ ትምህርት ቤቴ የሚለው ነው፡

- በመጀመሪያ ወላጆቼ በሚያገኙ ትምህርት ቤቴ ወስጥ እንድ የገጠሩ ህጻን ትምህርት ቤት ነው። እንዲሁ ትምህርት ቤቴ ወስጥ የእንስሳት የሆኑ መሥራቸው የሰው መማሪያው በእጅ የሚደረግ ቀጥታ የሰው ለምሳሌ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ ዳህዮች ቀርፀ ቅርፆች የተለያዩ በእጅን ለሚያዩት የሚገለፀው የሩቅት እንደምናያም ።።

በዚህ ም ትምህርት የተገኙ ለተማሪዎች በቅ ጓደኞች ለሚማሩት ሚ ለመምህር መምህር እንዲያገኙ ለመማሪያ ~~ወ~~ እንዲሁ እንደለጉም።። ብዙ ሀብታም ለሌሎች የሚያስተምሩ መሠረት የእኛ ምስራቅ ሃይማኖት ፡ የአገሪቱ ዕድ ፡ በቅ የጎሳ ና የዲሞክራሲ ቻርተር ወላጆቹ ይህ የድርሰት እይታ ስዕላዊ ድርሰት ነው

ሰላም ለሰው ልጆች

ሰላም ለሰው ልጆች በሙሉ አስፈላጊነቱ መሆኑ ግልጽ ነው።
ሰላም ካለ ብቻ የሰው ልጆች በፍቅር፣ በህብረት/በአንድነት በሰላም እንደሚኖሩ
ሰላም ባለበት የሰው ልጆች ሥራ ለመግባት፣ ሰርቶ ለመለወጥ እና ከእንስሳት
ጋር ለመኖር እና ሌላ እንዲሁም ለሰብዓዊ ፍጡር የሆነ ለሰው ልጆች
ሁሉ የሆነ ለሁሉም ተፈላጊ ነገር ሰላም አስፈላጊ መሆኑ
ነገር/መሠረት ነው!!

ሰላም ከሌለ ብቻ እኛ ከእኛ ጋር፣ ሰፈር ከሰፈር ጋር፣
መንግሥት ከመንግሥት ጋር፣ ሀገር ከሀገር ጋር፣
ጋር እምነት ከእምነት ጋር መዋጋት ለሰላም ሊሆን እንደማይችል ስለዚህ
ሰላም ለሰው ልጆች ለሁሉም በሙሉ አስፈላጊ መሆኑን ነገር ስለሆነ
ሰላም በሁሉም በሁሉም ቦታ ሰላም ያስፈልገናል!!

እናት ፍቅር

እናት ፍቅር ከሁሉ ፍቅር ይበልጣል:: እሷ ብዙ ስቃይ ይደርስባታል
ይወልዳት ነገር ግን እናት ፍቅር እንደምትን ይበልጣል. እናት ልጅ
ለመውለድ ብዙ ስቃይ እና ችግር ይደርስባታል እናት በልጇ ዘመን ሁሉ
ትንከባከባለች ትመግባለች ገንዘብ ለልጇ ታንከባክባለች ታስደስታለች::
የልብሱን ጉዳይ በትምህርቱ፣ በጤና፣ በሁሉ፣ በሁሉም፣
በሚያደርገው ሁሉ በሀገራት ሰርቶችን በስራም ሁሉም በሀገር ህይወት
ለማኖር ስራም፣ በአዳር በፍቅርም እናት ታደርጋለች::
የምትለው እናት፣ ወንድ፣ ሴት ዘመድ እንዲሁም ጎረቤት ለሁሉ ትረዳለች::
እናት ልጇ እንዲያድግ ስትል በደስታም እንደ ልጇ ታድላለች

በዚህ ዓለም እናት ፍቅር ይበልጣል እናት እንደምትሆን
የምትሰጠው ነገርን ሁሉ ለልጇ እንዲበለጽግ እናት ይኖር እናት እናት ነች::

ለተማሪዎች የቀረበ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ተገቢነት መገምገሚያ ቅጽ

የፈተናው ተገቢነት

ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ተገቢነት መገምገሚያ ቅጽ

የዚህ መገምገሚያ ቅጽ ዋና ዓላማ‹‹ እጩ መምህራን ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታን መፈተሽ›› በሚል ርዕስ ለሚካሄደው ጥናት በአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለሦስተኛ ዓመት ተመራቂ ዕጩ መምህራን የተዘጋጀ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ተገቢነት መፈተሽ ነው፡፡የዕርሶም ግምገማ ለፈተናው የተገቢነት ደረጃ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው ከዚህ በታች የቀረቡትን ሦስት ዝግና ሦስት ክፍት ጥያቄዎች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ላይ ነጻ አስተያየቶን እንዲሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ለሚያደርጉት ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡የቀረቡት መገምገሚያ መስፈርቶች አማራጭ አራት ናቸው፡፡1-ዝቅተኛ 2-መካከለኛ 3-ከፍተኛ 4-በጣም ከፍተኛ በሚል ተቀምጠዋል፡፡መልስዎን በመስፈርቱ ትይዩ በተሰጠው ቦታ የ‹‹ X ›› ምልክት ያስቀምጡ፤በቀጣይ ሦስት ጥያቄዎች ሀሳቦን በነጻነት ይግለጹ፡፡

የመገምገሚያ መስፈርቶች	4	3	2	1
1/ የቀረቡት መጻፊያ ርዕሶች(ምክንያቶች)ለዕጩ መምህራኑ ግልጽና አሻሚነት የሌላቸውና ጥሩ ሀሳብ ማፍለቅ የሚያስችሉ በመሆናቸው				
2/ የዕጩ መምህራኑን ማህበራዊ፣ሃይማኖታዊ፣ጾታዊና ዳራዊ እውቀት አንጻር ተገቢነት ያለው በመሆኑ				
3/ከመረሃ ትምህርትና ከመማሪያ ሞጁል አንጻር ተገቢነት ያለው በመሆኑ				

4/ ከዚህ በላይ የቀረቡትን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መገምገሚያ መስፈርቶች አንጻር የዕርስዎ ምላሽ‹‹ዝቅተኛ››ከሆነ ያሉበትን ምክንያት በመጥቀስ አማራጭ መፍትሄ ያስቀምጡ፡፡

5/ ከላይ የቀረቡት ድርሰት የመጻፍ ፈተና የቀረቡ ርዕሶች(ምክንያቶች)ለደረጃው የሚመጥኑ መሆን አለመሆናቸውን ያልዎትን አስተያየት ቢገልጹ፡፡

6/ የቀረቡትን የመጻፊያ ረዕሶች አስመልክቶ ሌሎች ሊሻሻሉ ይገባቸዋል የሚሏቸው ጉዳዮች ካሉ

ቢገልጹ፡፡

ምንጭ፡-ሃይላይ (2011) መነሻ

ያደረገ

በአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ለተመራቂ ዕጩ መምህራን ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ ለመወሰን የጠዘጋጀ ፈተና (25%)

ለፈተናው የተፈቀደው ሰዓት 2፡00

የተፈታኝ መለያ ቁጥር--------------------

ዕድሜ---------------------

ፆታ------------------------

የመጣበት/ችበት አከባቢ-------------ወረዳ----------ቀበሌ-----------

የጋቢቻ ሁኔታ----------------

የማትሪክ ውጤት-------------

አጠቃላይ መግለጫ

የዚህ ፈተና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ሀሳብን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታን መመዘን ነው፡፡ ለፈተናው ከተዘጋጁት 10 የመፃፊያ ርዕሶች/ምክንያቶች አንዱን በመምረጥ ከሁለት አንቀጽ ባልበለጠ፤ገላጭ/ተራኪ የድርሰት አፃፃፍን በመጠቀም ወይም በመከተል ድርሰት ፃፍ/ፊ፡፡ ድርሰቱ ነባራዊ ወይም ምናባዊ አቀራረብ ሊኖረው ይችላል፤ዋናው ሊገለጽ የተፈለገው ሀሳብ ለአንባቢ ግልፅና ለስሜቱ ቅርብ መሆን አለበት፡፡

ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና የቀረቡ የመጻፊያ ርዕሶች(ምክንያቶች)

ትምህርት ቤቴ

የእናት ፍቅር

ሙስናን ማስወገድ ላገር ያለው ፋይዳ

የልጅነት ህልሜ

የሀገር ፍቅር

የመስቀል በዓል አከባበር በደቡብ

የልባሙ ሊሲትሮ ህልም

ፍቅር የጀመረኝ 9ኛ ክፍል እንደገባሁ ነበር

ሰላም ለሰው ልጆች

የልብ ጓደኛ

ድርሰት የመፃፍ ችሎታ መመሪያዎችና መመዘኛ መስፈርት

ከዚህ ስር ሁለት ዓይነት ቅፆች ተቀምጠዋል።የመጀመሪያው ቅፅ የውጤት አሰጣጡን በተመለከተ ዝርዝር መመሪያዎችን ይዟል።ሁለተኛው ቅፅ በዝርዝር መመሪያዎቹ መሰረት የእያንዳንዱ ዕጩ መምህር ሀሳቡን በጽሑፍ የመግለፅ ችሎታ ውጤት መወሰኛ ሐሳቦችንና የውጤት መስጫ ሳጥን ይዟል።

እባክዎን መምህር በዝርዝር መመሪያው መሰረት የዕጩ መምህራኑን ውጤት በተሰጠው ሳጥን ውጤታቸውን በመሙላት ትብብራችሁን ስጠይቅ ለተደረገልኝ ትብብር ከወዲሁ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

1) **ድርሰት የመጻፍ ችሎታ መመዘኛ መመሪያዎች**

የድርሰት የመጻፍ ችሎታ የውጤት መወሰኛ መመሪያዎች	የውጤት ደረጃ
ይዘት	
የድርሰቱ አጠቃላይ ይዘት ግልጽ መልዕክትና የተመጣጠነ ርዝመት አለው፤ በጽሑፉ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችም ግልጽ፣ ጥልቅና በውል የታሰበባቸው ናቸው፤ የተወሰነ ዓላማና ትኩረት አላቸው።	5
ድርሰቱ ግልጽ መልዕክት ያለው ግን ውስን የሆኑ ክፍተቶች አሉበት፤ አብዛኞቹ ሐሳቦች ጥልቅና ግልጽ የሆኑና ከርዕሰጉዳዩ ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ግን ዝርዝር ሐሳቦች ይቀራሉ።	4
የድርሰቱ ሐሳቦች የርዕሰጉዳዩን መልዕክት የያዙ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ድግግሞሽና አላስፈላጊ ሐሳቦች ተካተዋል።	3
ድርሰቱ ግልጽ መልዕክት የለውም፤ አንባቢው የታወቀ አይደለም፤ የሐሳብ መዛባት አለበት፤በአንድ በታወቀ ሐሳብ የተጻፈ አይደልም፤ አንድን ሐሳብ አብስሎ ከማቅረብ ይልቅ ከዚያም ከዚያም ይዘላል፤ በበቂ ዐረፍተ ነገሮችና አገላለጾች አልተደገፈም፤ የተንዛዛና ግልጽነት የሌለው ነው።	2
የድርሰቱ ሐሳቦች ግልጽ አይደሉም፤ጠቃሚ ሐሳብም አልያዘም፤ መልዕክቱም	1

አይታወቅም፡፡	
የሀሳብ አደረጃጀት	
ድርሰቱ ግልጽ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ አንቀጾችን ይዟል፤ በያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ የሃይለቃልና የደጋፊ ዐረፍተነገሮች ተጠየቃዊ አቀማመጥ ትክክል ነው፡፡	5
የተወሰኑ ለመረዳት የሚያስቸግሩ የተቆራረጡ ሐሳቦች አሉ፤ በአንቀጾች ተከፋፍሎ ቢቀርብም በሃይለቃልና በደጋፊ ዐረፍተነገሮች መካከል የተጠየቃዊ ተገቢነት የለም፡፡	4
ድርሰቱ ግልጽ የሆነ የመግቢያና ማጠቃለያ አንቀጾች ያሉት ቢሆንም አላስፈላጊ ድግግሞሽ አሉት፤ በአንቀጾች በሃይለቃልና በደጋፊ ዐረፍተነገሮች ተጠየቃዊ አቀራረብ የላቸውም፤	3
ድርሰቱ ተጠየቃዊ የሐሳብ ፍሰት የለውም፤ አላስፈላጊ የሆኑ ወይም የተዛቡ መሸጋገሪያዎች አሉ፤ መግቢያ እያለው ማጠቃለያ የለውም፤ ወይም ማጠቃለያ እያለው መግቢያ የለውም፤	2
ድርሰቱ የሓሳብ ግጥምጥምነት የለውም፤ የሐሳብ አደረጃጀቱ አንባቢን ግራ ያጋባል፤ አያግባባም፡፡	1
የቃላት ምርጫና አጠቃቀም	
በድርሰቱ ውስጥ ያሉት ቃላት ምርጥና ተገቢ ናቸው፤ በምርጫም ሆነ ባጠቃቀም የተሻለ ነው፤ ግልጽነት የሌላቸውና አለቦታቸው የገቡ ቃለት የሉም፡፡	5
በቂ የቃላት ምርጫዎች አሉ፤ ግን የተወሰኑ የአጠቃቀም ችግሮች አሉ፤ አለቦታቸው የገቡ ቃላት ቢኖሩም ለመረዳት አይከብዱም፡፡	4
የተወሰኑ ቃላት ግልጽነት የሌላቸውና ፍቺያቸውን ለመረዳት ያስቸግራሉ፤ አለቦታቸው የገቡም አሉ፤	3
ብዙ ቃላት ትርጉም የሌላቸውና ለመረዳት የሚከብዱ ናቸው፤	2
አጠቃላይ የጽሑፉን ለመረዳት የማያስችሉና ምንም ትርጉም የሌላቸው ቃላት ይበዛሉ፤	1
የሰዋስው ትክክለኛነት	
የድርሰቱ ሀሳቦች በትክክለኛ ቃላትና የአረፍተ ነገሮች መቀየር ቀርቧል፤	5

አብዛኞቹ ሃሳቦች በትክክል ተዋቅሯል፤ውስን የሆኑ ባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ስምምነትና የቃላት አወቃቀር ችግሮች ብቻ ይታያሉ፡፡	4
ለተግባቦት በቂ ቢሆንም ቀላል የሚመስሉ የሰዋስው ስህተቶች አሉ፤	3
በርካታ አረፍተ ነገሮች ላይ ሰዋስዋዊ ስህተቶች አሉ፤በጣም ውስን የሆኑ ሀሳቦች ብቻ በትክክል ተዋቅሯል፡፡	2
በትክክል የተዋቀሩ ሀሳብ የለም፤በቃላትና በአረፍተ ነገሮች አወቃቀር ሰዋስዋዊ ስህተቶች የበዛሉ፤ ለመግባባት አያስችልም፡፡	1
የአጻጻፍ ስርዓት	
የድርሰቱ ቅርፅ ትክክል ነው፤በጣም ውስን የሆኑ የፊደላትን የሥርዓተ-ነጥብ ግድፈቶች አሉ፤	5
አልፎ አልፎ የቅርፅ፣የፊደላትና የሥርዓተ- ነጥብ ችግሮች አሉ፤	4
ተከታታይና ተደጋጋሚ የሆኑ የፊደላትና የሥርዓተ - ነጥብ ችግሮች አሉ፤	3
አብዘኛው የፅሁፍ ክፍል በቅርፅ፣በፊደላትና በሥርዓተ-ነጥብ ችግር የተሞላ ነው፡፡	2
ሥርዓተ አፃፃፍ ለመግባባት የሚያስችል አይደለም፡፡	1

2) ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ውጤት መመዘኛ ቅጽ

ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የውጤት መመዘኛ መስፈርቶች	ውጤት				
የድርሰቱ ይዘት የተወሰነ ዓላማና አንባቢ፣ ግልጽ መልዕክትና የተመጣጠነ ርዝመት አለው፤ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያሉ ሐሳቦች ወጥነትና ግልጽነት መረጃዎች ይዘዋል፤ የድርሰቱ ደጋፊ ሐሳቦች (ምሳሌዎች) ግልጽና አሳማኝ እውነታ አላቸው፡፡					
ድርሰቱ ግልጽና ተጠየቃዊ የሆነ አደረጃጀት አለው፤ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ አንቀጾችን ይዟል፤ የጽሑፉ መግቢያ (አጀማመር) የርዕሰጉዳዩን ሐሳብ በማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው፤ የማጠቃለያ አንቀጹም የጽሑፉ ጭምቅ ሐሳብ የያዘ ነው፤ በያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ የሃይለቃልና የደጋፊ ዐረፍተነገሮች ተጠየቃዊ አቀማመጥ ትክክል ነው፡፡					
በድርሰቱ ውስጥ ያሉት ቃላት ትክክል፣ ግልጽና በጥንቃቄ የተመረጡ ናቸው፤ በምርጫም ሆነ ባጠቃቀም ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው አዳዲስና አላስፈላጊ ቃላት የሉም፤ ግልጽነት የሌላቸውና አንባቢን ግራ የሚያጋቡ ቃላት የሉም፡፡					
በድርሰቱ የቃላትና የዐረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ አወቃቀር ስሕተቶች (ለምሳሌ፣ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽና የጾታ፣ ቁጥርና መደብ ስምምነቶች) በጣም ውስን ናቸው፤ በድርሰቱ የተንዛዙና የዐረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ችግሮች አይበዙም፡፡					
በድርሰቱ ውስጥ የሥርዓተነጥብ አጠቃቀምና የፊደላት ግድፈት እምብዛም ችግር የለም፤ የድርሰቱ ቅርጽ (መስመሮችና የዳር ህዳጎች) የተመጠኑ ናቸው፡፡					

የደረጃ መወሰኛ ዝርዝር መስፈርቶች

መስፈርቶች	ዝርዝር መስፈርቶች	ውጤት	ደረጃ
ይዘት (100%)	የድርሰቱ አጠቃላይ ይዘት ግልጽ መልዕክትና የተመጣጠነ ርዝመት ያለው፤ በጽሑፉ ውስጥ ያሉ ሐሳቦችም ግልጽ፣ ጥልቅና በውል የታሰበባቸው ከሆኑ፤ የተወሰነ ዓላማና ትኩረት ያላቸው።	80 -100	ከፍተኛ
	ድርሰቱ ግልጽ መልዕክት ያለው ግን ውስን የሆኑ ክፍተቶች ያሉበት፤ አብዛኞቹ ሐሳቦች ጥልቅና ግልጽ የሆኑና ከርዕሰጉዳዩ ጋር የተያያዙ ከሆኑ እና ዝርዝር ሐሳቦች የሚቀራቸው።	50 - 79	መካከለኛ
	የድርሰቱ ሐሳቦች የርዕሰጉዳዩን መልዕክት የያዙ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ድግግሞሽና አላስፈላጊ ሐሳቦች ያካተቱ።	20 - 49	ዝቅተኛ
	ድርሰቱ ግልጽ መልዕክት የሌለው፤የሐሳብ መዛባት ያለበት፤በአንድ በታወቀ ሐሳብ የተጻፈ ያይደለ፤ አንድን ሐሳብ አብስሎ ከማቅረብ ይልቅ ከዚያም ከዚያም የሚዘል፤ በበቂ ዐረፍተ ነገሮችና አገላለጾች ያልተደገፈ፤የተንዛዛና ግልጽነት የሌለው ከሆነ።	0 -19	በጣም ዝቅተኛ
የሀሳብ አደረጃጀት (100%)	ድርሰቱ ግልጽ መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ አንቀጾችን የያዘ፤በያንዳንዱ አንቀጽ ውስጥ የሃይለቃልና የደጋፊ ዐረፍተነገሮች ተጠየቃዊ አቀማመጥ ትክክል የሆነ።	80 -100	ከፍተኛ
	የተወሰኑ ለመረዳት የሚያስቸግሩ የተቆራርጡ ሐሳቦች ያሉት፤ በአንቀጾች ተከፋፍሎ ቢቀርብም በሃይለቃልና በደጋፊ ዐረፍተነገሮች መካከል የተጠየቃዊ ተገቢነት የሌለው።	50 - 79	መካከለኛ
	ድርሰቱ ግልጽ የሆነ የመግቢያና ማጠቃለያ አንቀጾች ያሉት ቢሆንም አላስፈላጊ ድግግሞሽ ያሉት፤በአንቀጾች በሃይለቃልና በደጋፊ ዐረፍተነገሮች ተጠየቃዊ አቀራረብ የሌላቸው ከሆነ፤	20 - 49	ዝቅተኛ
	ድርሰቱ ተጠየቃዊ የሐሳብ ፍሰት የሌለው፤አላስፈላጊ የሆኑ ወይም የተዛቡ መሸጋገሪያዎች ያሉት፤መግቢያ እያለው ማጠቃለያ የሌለው፤ወይም ማጠቃለያ እያለው መግቢያ የሌለው፤ለአንባቢ ግራ የሚያጋባ ከሆነ፤	0 -19	በጣም ዝቅተኛ
የቃላት አመራ	በድርሰቱ ውስጥ ያሉት ቃላት ምርጥና ተገቢነት ያላቸው፤ በምርጫም ሆነ ባጠቃቀም የተሻለ ከሆነ፤ ግልጽነት የሌላቸውና	80 -100	ከፍተኛ

	አለቦታቸው የገቡ ቃለት ያስወገደ ከሆነ፡፡		
	በቂ የቃላት ምርጫዎች ያሉት፤ ግን የተወሰኑ የአጠቃቀም ችግሮች የሚታዩበት፤ አለቦታቸው የገቡ ቃላት ቢኖሩም ለመረዳት የማይከብዱ ከሆነ፡፡	50 - 79	መካከለኛ
	የተወሰኑ ቃላት ግልጽነት የሌላቸውና ፍቺያቸውን ለመረዳት የሚያስ ቸግሩ፤ አለቦታቸው የገቡና ጽሁፉን ለመረዳት የሚያዳግቱ ቃላት ያሉት ከሆነ፤	20 - 49	ዝቅተኛ
	ብዙ ቃላት ትርጉም የሌላቸውና ለመረዳት የሚከብዱ ከሆነ፤	0 -19	በጣም ዝቅተኛ
የሰዋሰው ትክክለኛነት (100%)	የድርሰቱ ሀሳቦች በትክክለኛ ቃላትና የአረፍተ ነገሮች በመዋቀር የቀረቡ ከሆነ፤	80 -100	ከፍተኛ
	አብዛኞቹ ሀሳቦች በትክክል ተዋቅረው፤ውስን የሆኑ ባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ስምምነትና የቃላት አወቃቀር ችግሮች ብቻ የሚታይባቸው ከሆነ፡፡	50 - 79	መካከለኛ
	በርካታ አረፍተ ነገሮች ላይ ሰዋስዋዊ ስህተቶች አሉ፤በጣም ውስን የሆኑ ሀሳቦች ብቻ በትክክል ተዋቅሯል፡፡	20 - 49	ዝቅተኛ
	በትክክል የተዋቀሩ ሀሳብ የሌለው በቃላትና አረፍተነገሮች አወቃቀር ሰዋስዋዊ ስህተቶች የበዙና ለመግባባት አስቸጋሪ ከሆነ፡፡	0 -19	በጣም ዝቅተኛ
የአፃፃፍ ስርዓት (100%)	የድርሰቱ ቅርፅ በትክክል የተዋቀረ፤በጣም ውስን የሆኑ የፊደላትን የሥርዓተ-ነጥብ ግድፈቶች ካትሉ፤	80 -100	ከፍተኛ
	አልፎ አልፎ የቅርፅ፣የፊደላትና የሥርዓተ- ነጥብ ችግሮች ካሉት፤	50 - 79	መካከለኛ
	ተከታታይና ተደጋጋሚ የሆኑ የፊደላትና የሥርዓተ - ነጥብ ችግሮች ካሉት፤	20 - 49	ዝቅተኛ
	አብዘኛው የፅሁፍ ክፍል በቅርፅ፣በፊደላትና በሥርዓተ-ነጥብ ችግር የተሞላ ከሆነ፡፡	0 -19	በጣም ዝቅተኛ

ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ፈተና ውጤት

መለያ ቁጥር	ይዘት				የሀሳብ አደረጃጀት				ሰዋስው				የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም				ሥርዓተ አጻጻፍ			
	I	II	III	አማካይ	I	II	III	አማካይ	I	II	III	አማካይ	I	II	III	አማካይ	I	II	III	አማካይ
01	3.00	3.00	2.00	2.67	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	3.00	3.00	2.67	1.00	2.00	1.00	1.33	2.00	2.00	1.00	1.67
02	3.00	2.00	2.00	2.33	1.00	1.00	2.00	1.33	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	1.00	1.00	1.00
03	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	3.00	3.00	2.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	1.00	1.33
04	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	1.00	2.00	1.00	2.00	1.00	2.00	1.67	2.00	1.00	2.00	1.67
05	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	1.00	1.33	2.00	3.00	1.00	1.67	2.00	3.00	1.00	2.00	2.00	2.00	1.00	1.67
06	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.67	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	1.00	2.00	1.33
07	4.00	3.00	4.00	3.67	2.00	1.00	2.00	1.67	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	4.00	2.00	2.67	1.00	3.00	1.00	1.67
08	3.00	4.00	3.00	3.33	1.00	2.00	3.00	2.00	1.00	2.00	3.00	2.67	1.00	2.00	3.00	2.00	1.00	2.00	3.00	2.00
09	2.00	4.00	3.00	3.00	4.00	3.00	3.00	3.33	2.00	4.00	3.00	3.00	3.00	4.00	3.00	3.33	2.00	4.00	3.00	3.00
10	2.00	3.00	4.00	3.00	2.00	3.00	4.00	3.00	2.00	4.00	3.00	3.00	2.00	4.00	3.00	3.00	3.00	2.00	2.00	2.33
11	2.00	3.00	3.00	2.67	1.00	2.00	3.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	1.00	2.00	1.67
12	2.00	2.00	1.00	1.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	3.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	1.00	1.33
13	4.00	3.00	3.00	3.33	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	2.67	4.00	3.00	2.00	3.00	2.00	3.00	2.00	2.33
14	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	1.00	1.00	1.33	2.00	1.00	3.00	2.00	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	1.00	3.00	1.67
15	4.00	3.00	3.00	3.33	3.00	3.00	2.00	2.67	2.00	1.00	4.00	2.33	4.00	2.00	3.00	3.00	2.00	2.00	2.00	2.00
16	3.00	3.00	4.00	3.33	4.00	3.00	5.00	4.00	3.00	2.00	3.00	2.67	4.00	3.00	4.00	3.67	4.00	2.00	4.00	3.33
17	5.00	4.00	3.00	4.00	4.00	4.00	4.00	4.00	5.00	4.00	3.00	4.00	5.00	4.00	3.00	4.00	5.00	4.00	3.00	4.00
18	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	2.00	3.00	2.33	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	1.00	3.00	2.33
19	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	3.00	2.33	1.00	1.00	2.00	1.33	3.00	2.00	3.00	2.67	2.00	1.00	2.00	1.67
20	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	3.00	3.00	2.67	2.00	2.00	3.00	2.33
21	2.00	1.00	2.00	1.67	2.00	1.00	3.00	2.00	1.00	2.00	2.00	1.67	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	1.00	1.00	1.33

22	2.00	1.00	2.00	1.67	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	1.00	2.00	1.33	1.00	1.00	2.00	1.33	1.00	1.00	1.00	1.00
23	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	3.00	2.00	1.00	1.00	2.00	1.33	2.00	2.00	2.00	2.00
24	1.00	2.00	1.00	1.33	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	1.00	2.00	1.67	1.00	2.00	1.00	1.33	1.00	1.00	1.00	1.00
25	1.00	2.00	2.00	1.67	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	3.00	2.00	2.00	1.00	2.00	1.67	2.00	1.00	1.00	1.33
26	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	2.00	1.67	2.00	1.00	2.00	1.67	1.00	1.00	2.00	1.33
27	4.00	2.00	3.00	3.00	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	2.00	1.67	3.00	2.00	3.00	2.67	1.00	2.00	3.00	2.00
28	4.00	3.00	4.00	3.67	3.00	3.00	3.00	3.00	4.00	3.00	3.00	3.33	3.00	3.00	2.00	2.67	2.00	3.00	2.00	2.33
29	3.00	3.00	2.00	2.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	2.00	2.00	1.67	1.00	1.00	2.00	1.33	3.00	1.00	1.00	1.00
30	3.00	1.00	4.00	2.67	3.00	2.00	4.00	3.00	2.00	2.00	3.00	2.33	2.00	1.00	2.00	1.67	1.00	1.00	1.00	1.00
31	4.00	4.00	4.00	4.00	4.00	3.00	4.00	3.67	4.00	3.00	4.00	3.67	4.00	3.00	4.00	3.67	4.00	3.00	4.00	3.00
32	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	3.00	2.00	2.33	2.00	4.00	2.00	2.67
33	4.00	3.00	4.00	3.67	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	4.00	3.33	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	2.00	3.00	2.67
34	4.00	1.00	4.00	3.00	4.00	2.00	4.00	3.33	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	1.00	3.00	2.33	2.00	1.00	2.00	1.67
35	2.00	1.00	2.00	1.67	1.00	1.00	1.00	1.00	1.00	1.00	1.00	1.00	2.00	1.00	2.00	1.67	1.00	1.00	1.00	1.00
36	3.00	3.00	2.00	2.67	3.00	3.00	2.00	2.67	1.00	1.00	3.00	1.67	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00	2.00
37	4.00	3.00	4.00	3.67	3.00	2.00	3.00	2.67	4.00	3.00	4.00	3.67	3.00	2.00	2.00	2.33	2.00	2.00	2.00	2.00
38	1.00	2.00	1.00	1.33	2.00	2.00	2.00	2.00	3.00	2.00	3.00	2.67	2.00	2.00	2.00	2.00	1.00	2.00	1.00	1.33
39	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	3.00	3.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	3.00	3.00	3.00
40	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	3.00	3.00	3.00	4.00	3.00	2.00	3.00	3.00	2.00	3.00	2.67	3.00	2.00	3.00	2.67
41	1.00	2.00	1.00	1.67	1.00	2.00	1.00	1.33	1.00	2.00	1.00	1.33	2.00	1.00	1.00	1.33	1.00	2.00	1.00	1.33

ማስታወሻ ፡- አራሚ I

- አራሚ II

- አራሚ III

በምእራፍ አራት ውስጥ በውጤት ትንተናው ላይ በአጋዥነት የቀረበ የትንተና ውጤት አባሪ

ሀ/ የጽህፈት ንዑስ ክሂል ይዘት፣ስፋትና ጥልቀት በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ሲተነተን፡፡

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ-ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	2.66	0.737	1.452	40	0.156

ለ/ ከጽህፈት ንዑስ ክሂላን መካከል አንዱ የሀሳብ አደረጃጀት ሲሆን በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ተተንትኗል፡፡

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ -ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	2.414	0.726	-0.753	40	0.456

ሐ/ የጽህፈት ንዑስ ክሂል ሰዋስው ትክክለኛነት በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ሲተነተን፡፡

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ -ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	2.28	0.74	-1.859	40	0.070

መ/ የጽህፈት ንዑስ ችሎታ መካከል የቃላት አመሰራረጥና አጠቃቀም በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ሲተነተን፡፡

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ -ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	2.28	0.713	-1.925	40	0.061

ሠ/ የጽህፈት ንዑስ ክሂል ሥርዓተ አፃፃፍ በነጠላ ናሙና (one sample t-test) ሲተነተን፡፡

ናሙና (n)	አማካይ (m)	መደበኛ ልይይት (sd)	የቲ -ዋጋ T-Value	የነጻነት ደረጃ (df)	የጉልህነት ደረጃ (p)
41	1.90	0.7199	-5.0317	40	0.000